የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 11 ግንቦት 30/2015 ዓ.ም

# ሠርቶ መለወጥ እየቻለ ሠርቆ መለወጥ የሚያስብ ሰነፍ ትውልድ ተበራክቷል - ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ ዶ/ር



አገር አቀፍ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና የስራ ኃላፊዎች ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ሪፖርት ግምገማ ፎረም የክልል ሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮች፣ የፌደራል ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች በተገኙበት ተካሂዷል።

በመድረኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ፖሊሲ የዳሰሳ ጥናት፣ 21 ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናቶች፣ ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ያስገኘው ፋይዳ እና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እንዲሁም የዲጂታል ቴክኖሎጂ ለፀረ-ሙስና ትግል ያለው ፋይዳ የሚሉ አጀንዳዎች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል።

በመድረኩ የተገኙት ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እንደተናገሩት ብሔራዊ የስነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ፖሊሲ የሚስተዋሉ የሥነምግባር ዝንፈቶችን በተገቢው ለማረም እና የሙስና መከላከል ተግባራትን በአግባቡ ለመምራት የመነሻ ዳሰሳ ጥናት ሰነድ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው፥ ሌሎች ተጨማሪ ሰፊ ውይይቶች በማድረግ በቀጣይ ለማጽደቅ እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

ትውልዱ ሠርቶ መለወጥ እየቻለ ሠርቆ መለወጥ የሚያስብ ሆኗል ያሉት ኮሚሽነሩ፥ ሙስናን መሸከም የማይችል ህብረተሠብ በመፍጠር ረገድ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ሊረባረብ እንደሚገባ ገልፀዋል። ሙስናን ለመከላከል በመረጃ ላይ ተመስረተ መሆን ስለሚገባው ኮሚሽኑ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናቶች ማካሄዱን ጠቅሠዋል። የተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች የስነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ስራቸውን በማጠናከር ሚናችሁን መወጣት



እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል።

በነበረው የሁለት ቀን ውይይት በቀረቡት አጀንዳዎች ተጨማሪ ግብዓት መገኘቱን በመግለፅ በቀጣይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶች እንደሚካሄዱ አንስተዋል።

ማህበረሰቡ በተዘረጋው የዲጂታል ጥቆማ ሥርዓት ሙሰኞችን በመጠቆም ለፀረ-ሙስና ትግሉ ሚናውን እንዲወጣም ጥሪ አቅርበዋል።

የሙስና መከላከል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው በበኩላቸው በሁለት ቀን ቆይታ በሙስና ስጋት ጥናት፣ ብሔራዊ የስነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ፖሊሲ እንዲሁም በዲጂታል ጥቆማ አሰራር ስርዓት በርካታ ጠቃሚ ግብዓት መገኘቱን ጠቁመው፥ ሙስና በአለም ላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መዛባትን በመፍጠር ለሀገራት እድገት እንቅፋት መሆኑን ጠቅሰዋል።

በተለይ በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ፖለቲካዊ ቀውስ በመፍጠር እየፈተናቸው እንደሚገኝ ጠቅሰው፥ ብዙዎች የአፍሪካ ሀገራት የፀረ-ሙስና ፖሊሲ የሌላቸው ሲሆን፥ ከሌላቸው ሀገራት ደግሞ አንዷ ኢትዮጵያዊ እንደነበረች አስታውሰው፥ በኮሚሽኑ ብሔራዊ የስነምግባር ግንባታ እና የፀረ-ሙስና ፖሊሲ ዳሰሳ ጥናት ተዘጋጅቶ በዚሁ መድረክ በቂ ግብዓት መሰብሰቡን አንስተዋል። መድረኩ በርካታ ግብዓት የተሰበሰበበት እና ስኬታማ ሲሆን፥ በቀጣይ ተጨማሪ ውይይቶችን በማድረግ ሰነዶችን የማዳበር ስራ የሚቀጥል ይሆናል።

## በኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ከ6 ሺህ 500 ብር በታች በሆነ ወጪ መጨረስ ለሚቻለው ፓስፖርት እስከ 40 ሺህ ብር ጉቦ እየተጠየቀ መሆኑን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የምርመራ ዘገባ አጋለጠ

ገጽ 2

## በሲዳማ ክልል በሙስና ወንጀል የተከሰሱ 136 አመራሮችና ባለሙያዎች በእስራት እንዲቀጡ ተወሰነ

ገጽ 3

## ኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ስልጠና

### ጥራትና ተገቢነት ማሻሻያ ውይይት አካሄደ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሻሻሉ ሰባት የሙስና መከላከል እና ስድስት የሥነምግባር ግንባታ የስልጠና ሞጁሎች ላይ ጥራትና ተገቢነት የማሻሻያ ውይይት አካሂዷል። ሞጁሎቹ በአማካሪ ዶክተሮች ሙያዊ አስተያየቶች የተሰጠባቸው ሲሆን፥ በውይይት መድረኩ ተጨማሪ ተገቢ ግብዓት ለማከል ታሳቢ የተደረገ መሆኑን የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ዳግም አላምረው አስታውሰዋል።

ለሁለት ቀናት በተካሄደው የግብዓት ማሰባሰቢያ

ኮሚሽኑ የሥነምግባር... ወደ ገጽ 3 የዞረ

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

## በአገልግሎት አሰጣጥና በተቋማዊ አሰራር ጥናት ዙሪያ ውይይት አካሄደ





የአብክመ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በክልሉ ውስጥ ያሉ ብልሹ አሰራሮችንና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለማስተካከል ከአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ አመራሮችና ሰራተኞች ጋር በአገልግሎት አሰጣጥና በተቋማዊ አሰራር ጥናት ዙሪያ ውይይት አካሂዷል።

በአብክመ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ዳይሬክቶሬት ከገቢዎች ቢሮ በአገልግሎት አሰጣጥና በተቋማዊ አሰራር ዙሪያ ባካሄደው ጥናት መሰረት፥ በተገኙ የጥናት ግኝቶች ዙሪያ ከተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች ጋር ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል።

የአብክመ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ በተቋሙ ዙሪያ የቀረበው ጥናት ችግር ፈችና የመደጋገፍ ዓላማን ትኩረት ያደረገ ነው፥ እንደ መንግስት ያሉ ክፍተቶችን በውይይት ተደጋግፈን ቶሎ ማስተካከል እንዲቻል እና ለቀጣይ መስተካከል የማይችሉ ወጣ ያሉ በብልሹ አሰራሮችና በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የስነምግባር ጥሰት የሚያደርሱ ግለሰቦችን በህግ አግባብ ተጠያቂነትን ለማስፈን ጭምር ነው ብለዋል።

የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ ኋላፊ ዶ/ር ፀጋ ጥበቡ በበኩላቸው፥ የኮሚሽኑ አጥኝዎች ይህንን ጥናት ያካሄዱበት መንገድ የተቋማችን አሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ያዩበት እና ያልሰሩበትን ተቋም በዚህ ልክ መግለፅ መቻላቸው አጥኝዎች ሊመሰገኑ ይገባል፥ ለቀጣይ ግን ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት በመጀመሪያ ቁጭ ብለን በጥናቱ ዙሪያ መነጋገር ብንችልና የጋራ መግባባት ቢኖር ጥናቱን የበለጠ ሙሉ የሚያደርግ እና ችግሮችን መቅረፍ የሚችል የተዋጣለት ጥናት ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

አንድ ጥናት ከሌሎች የሚለየው ዳታን መሰረት ያደረገ መሆኑን አውስተው፥ አንድ አጥኝ አካል መረጃ ሲሰበስብ ትክክለኛ፣ ከስሜትና ከጥላቻ የፀዳ፣ ታማኝ እና ስለተቋሙ አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥ በቅርበት እውቅና ካለው ወይም ትክክለኛ የመረጃ ምንጭ በሆነ አካል ሊሆን ይገባል ብለዋል። ምክንያቱም ይህ የጥናት ውጤት የሚወሰነው በየትኛውም መልኩ አጥኝው በሰበሰበው ዳታ ልክ ስለሆነ፥ ጥናቱ ነገ መረጃ ለሚፈልግ አካል እንደ ሰነድ ሁኖ ማገልገል እንዲችል መረጃ አሰባሰብ ላይ ስልታዊና ጥንቃቄ የተሞላበት እንዲሁም የዳታ ጥራቱና እውነተኛነቱ ላይ ትኩረት ቢደረግበት ጥሩ ነው፤ የኮሚሽኑ ድጋፍና ክትትል ግን ሊቀጥል ይገባል በማለት አስተያየታቸውን ሰጠዋል። በመድረኩም የክልልና የዞን ገቢዎች ቢሮ እና የኮሚሽኑ አመራሮች እንዲሁም ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

በሌላ በኩል ኮሚሽኑ በሥነምግባር ግንባታናና ግብረ ገብነት ዙሪያ ያሠለጠናቸውን የባሕርዳር ከተማ ጣና ሐይቅ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አስመርቋል። ሥልጠናው "በላቀ የሥነምግባር ግንባታ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር የጸዳ ትውልድ እንፍጠር" በሚል መሪ ሃሳብ ሲሰጥ ቆይቷል። ሥልጠና የወሰዱ 25 ሴቶች እና አምስት ወንዶች በድምሩ 30 ተማሪዎች ተመርቀዋል። ሠልጣኝ ተማሪዎች ያገኙትን ዕውቀት የሚለካ ፈተና ወስደው እንደተመረቁም ተናግረዋል።

በዕለቱ የተመረቁት ተማሪዎች ሁለተኛ ዙር ሰልጣኞች ሲሆኑ ኮሚሽኑ በመጀመሪያው ዙር ሥልጠና የሰጣቸው 32 ተማሪዎች "ኢትዮጵያዊ የሥነምግባር እና የግብረ ገብ ማኅበር" መስርተው በክልሉ መንግሥት የዕውቅና ፈቃድ አግኝተው በመንቀሳቀስ ላይ መኾናቸው ተገልጧል።

ICS
የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት
IMMIGRATION AND CITIZENSHIP SERVICE

# በኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት

## ከ6 ሺህ 500 ብር በታች በሆነ ወጪ መጨረስ ለሚቻለው ፓስፖርት እስከ 40 ሺህ ብር ጉቦ እየተጠየቀ መሆኑን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የምርመራ ዘገባ አጋለጠ

የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት በፓስፖርት እድሳት እና ከአስቸኳይ ፓስፖርት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ዜጎች ለሕገ-ወጥ አሠራር ተጋላጭ ሆነው በሕጋዊ መንገድ ከ6 ሺህ 500 ብር በታች በሆነ ወጪ መጨረስ የሚችሉትን ፓስፖርት እስከ 40 ሺህ ብር በመክፈል አገልግሎት እንዲያገኙ ስለሚደረግበት ሂደት የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በምርመራ ጋዜጠኝነት ማረጋገጥ ችሏል።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ባደረገው የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራ ይህንኑ እውነታ ለአገልግሎቱ ሕገ-ወጥ ክፍያ እንዲከፍሉ ከተጠየቁ እንዲሁም ከከፈሉ ከዚያ ባለፈም በተቋሙ አካባቢ በመገኘት የሕገ-ወጥ አሠራሩን ሀገራዊ ይዘት አሳይቷል።

የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት ዋና ዳሬክተር አቶ ብሩህተስፋ ሙሉጌታ እንደገለጹት፥ ተቋሙ ከ33 በላይ ሠራተኞች ላይ የሥነ-ምግባር እርምጃ ቢወስድም ዛሬም ግን በሙስና እና በብልሹ አሠራር እየተፈተነ ነው።

አገልግሎቱን ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥረቶች በዘለለ ዜጎች በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጡ ዙሪያ ቅሬታ ካላቸውም ከቅሬታ ሰሚ ዴስክ አንሥቶ እስከ ተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ድረስ በመገናኘት ቅሬታቸውን ቢያሰሙ ተቋማቸው እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ እንደሆነ አቶ ብሩህተስፋ ሙሉጌታ ተናግረዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትም 95 በመቶ የሚሆነው ከፓስፖርት ሕትመት ጋር ተያይዞ ያሉ ግብዓቶች ጭምር በሀገር ውስጥ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ሥራዎች መጠናቀቃቸውን ገልጸዋል።

አገልግሎቱ እንዲጓደል የሚያደርጉ የተቋሙ ሠራተኞች ተቋሙ በቅርብ በሚካሄደው የአደረጃጀት ሪፎርም ላይ እንደሚጋለጡ እና እርምጃ እንደሚወሰድባቸው ነው የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት ዋና ዳሬክተር አቶ ብሩህተስፋ ሙሉጌታ ያረጋገጡት።





መንግሥት የጀመረውን ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ትግል በተገቢው መረጃና ማስረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የዜጎች ተሳትፎ ወሳኝ ነው።

በየአካባቢው የሚገኙ የማህበረሰብ አንቂዎች ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን መረጃ እና ማስረጃ በማመንጨት የፀረ-ሙስና ትግሉን እንድትደግፉ እና ከኮሚሽኑ ጋር የተደራጀ አገራዊ ህብረት እንድትመሠርቱ ጥሪ እናቀርባለን።

**መረጃ እና ዕውቀት-መር የፀረ-ሙስና ትግል ለማካሄድ የዲጂታል ቴክኖሎጂን እንጠቀም ፎቶና ቪድዮን ጨምሮ የሙስና እና ብልሹ አሠራር መረጃ በየትኛውም ቦታ ሆኖ በhttps://epfs.gov.et/ ይጠቁሙ፣ ይሸለሙ!**

# የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በኡጋንዳ ኢንቴቤ የምሥራቅ አፍሪካ ልማት በይነ መንግስታት (ኢጋድ) ባዘጋጀው የፀረ-ሙስና ጥምረት ወርክሾፕ ተሳተፉ

በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የኮሚሽነር ጽ/ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፣ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ገዛሐኝ ጋሻው እንዲሁም የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ስልጠና መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ዳግም አላምረው በኡጋንዳ ኢንቴቤ የምሥራቅ አፍሪካ ልማት በይነ መንግስታት (ኢጋድ) ባዘጋጀው የፀረ-ሙስና ጥምረት ወርክሾፕ ተሳተፉ።

ወርክሾፑ ከግንቦት 24-26 /2015 ዓ.ም ለተከታታ ሦስት ቀናት የተካሄደ ሲሆን፥ አባል ሀገራቱ የፀረ-ሙስና ትግሉን ማጠናከር እንዲችሉ፣ የአፍሪካ ሕብረት የሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እንዲሁም በፀረ-ሙስና ትግሉ የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮት እና በቀጣይም በሚወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ ማድረግ መቻላቸውን በመድረኩ ተሳታፊ የሆኑ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል።




## ኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ እና...

ውይይት የተገኙት አቶ ወዶ አጦ በኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ኮሚሽኑ በርካታ የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን፥ ለአብነትም የስነምግባር ግንባታ ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል የማሠልጠኛ ሞጁሎችን ጥራትና ተገቢነታቸውን በጠበቀ መልኩ የማሻሻል ስራ ማከናወን ተችሏል ብለዋል። የቡድን ውይይቶችን በማድረግ በቂ ግብዓት መወሰድ መቻሉን ገልፀዋል። የተነሱ ሃሳቦችን በማከል የሥልጠና ጥራተና ተገቢነት ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ ይሰራልም ብለዋል።

በመድረኩ ብዙ አቅም ያለው የሰው ኃይል ስለተሳተፈበት በቂ ሃሳብ መያዝ መቻሉን የተናገሩት ም/ኮሚሽነሩ፥ የተነሱ ኃሳቦች በአግባቡ ተገምግመው እንደአግባብነታቸው ጥቅም ላይ እንደሚውሉ በአፅንኦት ገልፀዋል። በውይይቱ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች፣ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ የተውጣጡ ምሁራን እና አግባብነት ያላቸው የፌዴራል መንግስት ተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል።







## አዲስ የተደራጀው የመሠረተልማት ግልጽነት ኢትዮጵያ መደበኛ ስብሰባውን አካሄደ

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የበላይ ጠባቂ ሁኖ የተቋቋመው የሥራ አመራር ቦርዱ የመንግሥት፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የግሉን ዘርፍ ያካተተ ነው።

የዓለምአቀፉ የመሠረተ ልማት ግልጽነት ኢኒሴቲቭ አባል የሆነው የኢትዮጵያ የመሠረተ ልማት ግልጽነት ኢኒሴቲቭ ዋና ዓላማው የኮንስትራክሽን ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሠራር የፀዳ፣ በዘርፉ ኢንዱስትሪ ጤናማ የገበያ ውድድር እንዲኖር የግልጽነት መረጃ ማመንጨት እና ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ ነው።

በመሆኑም፣ መንግሥት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚያፈስበት እና ውስብስብነት ያለው ዘርፍ በመሆኑ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እና ሙስና የፕሮጀክት ተግባራትን እንዳያደናቅፍ ከግዥ ጀምሮ እስከ ፕሮጀክት ትግበራ ምዕራፎች ያለውን መረጃ ነፃና ገለልተኛ በሆነ አቋም ጥናት በማድረግ የግልጽነትና የተጠያቂነትን አሠራር ሥርዓት እንዲጎለብት ማስቻል ነው።

## በሲዳማ ክልል በሙስና ወንጀል የተከሰሱ 136 አመራሮችና ባለሙያዎች በእስራት እንዲቀጡ ተወሰነ

በሲዳማ ክልል በሙስና ወንጀል የተከሰሱ 136 አመራሮችና ባለሙያዎች እስከ 11 ዓመት በሚደርስ እስራት እንዲቀጡ መወሰኑን የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አስታወቀ። ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ የተመዘበረ የመንግስትና የህዝብ ሀብት ማስመለስ መቻሉም ተገልጿል።

የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቶ ማሩ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፥ ሙስናና ብልሹ አሰራር ለልማትና ለመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ እንዳይቀጥል ለማድረግ እየተሰራ ነው። የክልሉ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የፀረ-ሙስና ክልላዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ ባደረገው እንቅስቃሴ ውጤት መገኘቱንም ገልጸዋል።

ኮሚቴው የሙስናን ወንጀል የመለየትና የምርመራ ሥራዎችን በዝግጅት ምዕራፍ መስራቱን ጠቅሰው፥ “በዚህም 118 ጥቆማዎች ከህብረተሰቡ ለመሰብሰብ ተችሏል” ብለዋል። ጥቆማዎቹ በገቢ፣ በፋይናንስና በመንግሥት ቤቶች አስተዳደር እንዲሁም ከኢንቨስትመንት አገልግሎት አሰጣጥና ከመሬት ጋር በተያያዘ ሙስናና ብልሹ አሰራር መፈጸማቸውን የሚያመላክቱ መሆናቸውን ገልጸዋል። “በየደረጃው ካሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የተገኙትን ጥቆማዎች በማደራጀትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት የምርመራ ሥራ ሰርተናል” ብለዋል።

የፀረ-ሙስና ክልላዊ ኮሚቴው በ265 መዝገቦች አደራጅቶ ምርመራና ክስ መመስረቱን ገልጸው፥ “ከነዚህ መዝገቦች ውስጥ 72 መዝገቦች በፍርድ ቤት ውሳኔ አግኝተዋል” ብለዋል። በምርመራ ሂደት 505 አመራሮች እና ባለሙያዎች እንዲጠየቁ ተለይተው፥ እስካሁን በ136ቱ ላይ ከአንድ ዓመት እስከ 11 ዓመት በሚደርስ የእስር ቅጣት እንዲቀጡ መወሰኑን ገልጸዋል። ከእስራት በተጨማሪ የተመዘበረ የህዝብ ሀብት ለማስመለስ በተደረገ ርብርብ ባለፉት ሦስት ወራት በክስና ምርመራ ሂደት ውስጥ በአጠቃላይ ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ የተመዘበረ ሀብት



እንዲመልሱ መደረጉንም ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ገልጸዋል።

በተለይ በሀዋሳ፣ በይርጋለም፣ በለኩና ሆኮ ከተሞች በህገ ወጥ መንገድ ለግለሰቦች ተላልፎ የነበረ ከአምስት ሄክታር በላይ መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ መደረጉን ያወሱት ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ፥ በፀረ-ሙስና ንቅናቄው የተሻለ ውጤት እየተመዘገበበት መሆኑንም አመልክተዋል። “ህገ ወጥ የትምህርት ማስረጃን ማዘጋጀትና መጠቀምን አስመልክቶ በደረሰ ጥቆማ መሠረት የቅጥርና የሥራ ዝውውርን ማስቆም ተችሏል” ሲሉም ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት በ193 መዝገቦች ክሳቸው እየታየ የሚገኙት የቀሪዎቹ 369 አመራሮችና ባለሙያዎችም ጉዳይ በክስ ሂደት ላይ መሆኑንም ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቶ አስታውቀዋል።

ህብረተሰቡ የሙስና ወንጀል በሀገርና በህዝብ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ተረድቶ በባለቤትነት መንፈስ ችግሩን ለመከላከል እያደረገ ያለውን ተሳትፎ አድንቀው፥ ተሳትፎውን እንዲያጠናክር ጠይቀዋል። እስካሁን ድረስ ለጠቋሚዎች በተደረገ የህግ ከለላ በማንም ላይ የደረሰ ተጽዕኖና በደል እንደሌለም ተናግረዋል። የእስር ቅጣት የተፈረደባቸው በክልል፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች መሆናቸውም ገልፀዋል።



# የትምህርት ሚኒስቴር

## ትክክለኛነታቸው እንዲረጋገጥ ከቀረቡለት የትምህርት ማስረጃዎች 40 በመቶ ሀሰተኛ ሆነው መገኘታቸውን አስታወቀ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት 18 ሽህ የትምህር ማስረጃዎች ትክክለኛነቱ ተፈትሾ 921 (አምስት በመቶዎቹ) ህገ-ወጥ ሆነው መገኘታቸውን አስታውቋል።

ቀጣሪ ተቋማት ለሚንስቴሩ ይረጋገጥልን ብለው ባቀረቡት ጥያቄ ደግሞ 225 የትምህርት ማስረጃዎች ተመርምረው 40 በመቶዎቹ ሀሰተኛ ሆነው መገኘታቸውንም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

ትምህርት ሚንስቴር የዘጠኝ ወር ሪፖርቱን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲያቀርብ፥ አባላቱ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በስፋት መሰራጨት እንዳሳሰበው ተናግረዋል። ገዙ ምናዬ የተባሉ የምክር ቤት አባል “በአንዳንድ የግል የትምህርት ተቋማት የሚወጡ የሀሰት የትምህርት ማስረጃዎች በስፋት እየተሰራጩ ስለሆነና ይህም በሀገር አሉታዊ ጫና ስላለው እነዚህን ተቋማት እውቅና ከማሳጣት አንፃር ምን እየተሰራ ይገኛል?” ሲሉ ጠይቀዋል።

የትምህርት ማስረጃ ማጣራትን ከራሳችን ጀምረናል ያሉት የትምህርት ሚንስትሩ ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)፥ በዚህ ዓመት ሁሉም የፌደራል ተቋማት ሰራተኞች ማስረጃ እንደሚጣራ ገልጸዋል።

ሚንስትሩ አክለውም በሁሉም የፌደራል ተቋማት የሰራተኞችን ማህደር መመርመር ጀምረናል፥ ምን ያህሉ እውነተኛ የትምህርት ማስረጃ ይዞ ነው? ምን ያህሉ አይደለም የሚል ከራሳችን ጀምረን ምርመራ እያካሄድን ነው ብለዋል። ማህበረሰቡ ልክ እንደ 12ተኛ ክፍል ፈተናው እንዲያውቅልን የምንፈልገው ከአሁን በኋላ በተጭበረበረ ድግሪ፣ በተጭበረበረ ዲፕሎማ የሚሰራ ስራ አይኖርም የሚለውን ለማሳወቅ ነዉ። በዚህ ዓመት እሱን እንጨርሳለን ብለን እናስባለን ብለዋል።

ይህን ለማድረግ ችግሩን ያልደበቁት ሚንስትሩ “ችግሩ ግን የሚታወቅ ነው፥ ሀገሩ የደላላ ሆኗል፤ ቀጥተኛ የሆነ የግብይት ስርዓትና ንፁህ የሆነ ስራን ለመስራት በጣም ብዙ ስራ ይቀረናል” በማለት መናገራቸውን አል ዓይን አማረኛ ዘግቧል። በ2015 ዓመት የሁሉም የፌደራል ተቋማት ሰራተኞች የትምህርት ማስረጃ ትክክለኛነት እንደሚረጋገጥ ሚንስትሩ አስታውቋል።

በተመሳሳ ዜና የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ማጣራት እንዲደረግባቸው በተለያዩ ተቋማት ከቀረቡለት የትምህርት ማስረጃዎች ውስጥ እስካሁን 21 ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች ማግኘቱን አሳውቋል።

ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ተቋማት የግለሰቦች የትምህርት ማስረጃ ተገቢነት ተጣርቶ እና ተረጋግጦ እንዲገለጽ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት በ42 የትምህርት ማስረጃዎች ላይ በሁለት ዙር ባካሄደው የህጋዊነት ማረጋገጫ ሥራ 21ዱ ሐሰተኛ ሆነው መገኘታቸውን የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር አሳውቋል።

ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃው በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ስም ተጭበርብሮ በተሰራ ማሕተም፣ በአመራር የስምና የማዕረግ ቲተር እንዲሁም በሐሰተኛ ፊርማ ተመሳስሎ የተሠራ መሆኑ ተመላክቷል።

ግለሰቦቹ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በመጠቀም በተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመምህርነት ተቀጥረው በመስራት የማይገባቸውን ጥቅም እያገኙ መሆኑም ተገልጿል። ዩኒቨርሲቲው የሐሰተኛ ትምህርት አጣሪ ግብረ ኃይል አቋቁሞ ሰፊ የማጣራት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ገልጿል።

# ከሙስና በፀዳ መንገድ ህብረተሰቡን ለማገልገል መዘጋጀታቸውን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አመራሮች ገለፁ

ከሙስና በፀዳ መንገድ ህብረተሰቡን በማገልገል የተፈጥሮ ሃብቱን ተጠቅሞ እንዲለወጥ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የዞንና የአሶሳ ከተማ አስተዳደር አመራሮች ተናገሩ።

ለአንድ ሳምንት በተሰተው የአቅም ግንባታ ስልጠና ላይ ከተሳተፉ አመራሮች መካከል ከአሶሳ ዞን የመጡት ወ/ሮ ሁዳ ከድር በሰጡት አስተያየት ህዝብን ማገልገል ታላቅ ሃላፊነት መሆኑን ገልጸዋል። የተፈጥሮ ሃብት በሚገባ ካለማ የማህበረሰቡ ህይወት ስለማይለውጥ በተለይ ከሌብነት የፀዳ አካሄድን በመከተል ህዝብን ማገልገል ግዴታችን ነው ብለዋል።

ይህም የተፈጥሮ ፀጋን ይዞ በድህነት መቆየትን በማስቀረት ለማህበረሰቡ ብሎም ለሃገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ እንደሆነ ጠቁመዋል። ስልጠናው አቅማችንን በሚገባ ገንብቷል ያሉት አስተያየት ሰጪዎች ከዚህ ውስጥ ከህዝብ ተቀራርቦ መስራት አንዱ እና ዋነኛው መሆኑን ተናግረዋል። የመተከል ዞን አመራር አቶ አንድነት በየነ በበኩላቸው፥ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ የኢንቨስትመንትና ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶች መገኛ የሆነው ዞኑ የልማት ኮሪደር እየሆነ መምጣቱን ገልጸዋል። በልማት ኮሪደሮች ፈታኝ ሁኔታዎች መከሰታቸው የሚጠበቅ ነው፥ ይህንን እንዴት ማለፍ እንዳለብን ስልጠናው ጠንካራ አቅጣጫ አመላክቷል ብለዋል።





ክልሉን ብሎም ሃገርን ከድህነት ከሚያላቅቁ ተቋማት የቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት አንዱ ነው ያሉት የካማሽ ዞን አመራር አቶ ዘላለም ደሬሳ ናቸው። በዘርፉ ስልጠና የሚወስዱትን በስራ እድል ፈጠራ ላይ በማሰማራት ለውጥ ማምጣት የቀጣይ ትኩረታቸው እንደሚሆን ገልጸዋል። ከዚህ ቀደም ባላቸው አቅም ልክ ህዝብን እንዳላገለገሉ የተናገሩት አመራሩ በዚህ ስልጠና በቁጭት ራሴን በመቀየር ማህረሰቡን ለመደገፍና ለማገልገል ተዘጋጅቻለሁ ብለዋል።

የአሶሳ ከተማ አስተዳደር አመራር አቶ አህመድ ከማል አሶሳ ከተማ እየሰፋ መምጣቱን ተከትሎ የህብረተሰቡ ጥያቄ መጨመሩን ገልጸዋል። የህብረተሰቡን ጥያቄ ለመመለስ የሚያጋጥሙ ፈታኝ ሁኔታዎችን ወደ እድል ከመቀየር ጀምሮ ውጤታማ ስራዎች ለማከናወን መዘጋጀታቸውን ገልፀዋል።

# የኮሚሽኑ አመራሮች እና ሰራተኞች በ2015 በጀት ዓመት የመንግሥት ዕቅድ የዘጠኝ ወራት ዋና ዋና አፈጻጸሞችን ውይይት አድረጉ

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች እና ሰራተኞች በ2015 በጀት ዓመት የመንግሥት ዕቅድ የዘጠኝ ወራት ዋና ዋና አፈጻጸሞችን በተመለከተ ሪፖርት ቀርቦ ውይይት አድርገዋል።

በተጨማሪም የኮሚሽኑን የቀሪ ወራት ተግባራት የትኩረት ጉዳዮች ላይ ርብርብ ለማድረግ የጋራ አቅጣጫ አስቀምጠዋል።







# የክልሉ አመራር ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የህዝብን ጥቅም ሊያስከብር እንደሚገባ ርዕሰ መስተዳድር ኦርዲን በድሪ ገለፁ

የክልሉ አመራር ሙስና፣ ሌብነትና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የህዝብን ጥቅም ሊያስከብር ይገባል ሲሉ የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ኦርዲን በድሪ አሳሰቡ።

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለአንድ ቀን ያካሄደው የሴክተር መስሪያ ቤቶች የ100 ቀን የስራ እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተጠናቅቋል። ርዕሰ መስተዳድሩ በወቅቱ፥ አመራሩ በክልሉ የሚገኙ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የሰላም ግንባታ ስራዎችን ከማጎልበት አንጻር ባከናወነው ስራ አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸውን ተናግረዋል።

በተለይ በክልሉ የዋጋ ንረት ችግርን ከማቃለል፣ ለዜጎች የስራ እድል ከመፍጠር፣ ሰላምና ጸጥታን ከማረጋገጥ፣ ምርትና ምርታማነትን ከማጎልበት አንጻር እየተከናወኑ የሚገኙ ስራዎች ውጤት እያስገኙ መሆናቸው ገልጸዋል። በእቅዱ ጠንካራ አሰራሮች ቢፈጠሩም በተለይ በክልሉ ህገ ወጥ የመሬት ወረራና የቤት ግንባታ መበራከቱን ጠቁመው፥ በዚህ ላይ አመራሩ ተቀናጅቶ መሰራት ይገባል ሲሉ አመልክተዋል።

በክልሉ በየደረጃው ያለው አመራር በተለይ ሙስና፣ ሌብነትና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የህዝብ ጥቅም ሊያስከብር እንደሚገባ ማሳሰባቸውን ኢዜአ ዘግቧል። በተለይ ምርትና ምርታማነትን በማጎልበት የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ከማጎልበት አንጻር እየተከናወኑ የሚገኙ ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውም አመልክተዋል።





# ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በሕግ ብቻ ሳይሆን ራስን በመለወጥና ህሊናን ዳኛ በማድረግ መታገል እንደሚገባ የሃይማኖት መምህር እና የታክስ አምባሳደር ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ ተናገሩ

በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የገቢው ዘርፍ ዋነኛ ተግዳሮት የሆነውን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እንዲቻል የስነምግባር ችግሮች እንዳይከሰቱ የሚረዳ ስልጠና እየሰጠ እንደሚገኝ በቅ/ ጽ/ቤቱ የታክስ ስርዓት ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ እቴነሽ ደሱ ተናግረዋል።

ዘወትር ወር በገባ በሁለተኛው ሰኞ በሚሰጠው በዚህ ስልጠና የቅ/ጽ/ቤቱ አመራርና ሰራተኞች ተሳታፊ ሲሆኑ፥ ከስልጠናው ጋር በማያያዝም ቀኑ የስነምግባር ቀን ተብሎ "ሙስናን መታገል በተግባር" በሚል መሪ ቃል ይከበራል። በእለቱ የተለያዩ የሙያ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ታዋቂ ሰዎችና ተቀባይነት ያላቸው ግለሰቦች፣ የሃይማኖት መምህራንና የሚ/ር መ/ቤቱ የታክስ አምባሳደሮች ልምድና ተሞክሮዎቻቸውን ያካፍሉበታል።

በዕለቱ መድረክ የሃይማኖት መምህርና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ታክስ አምባሳደር የሆኑት ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ እና የሜቄዶንያ በጎ አድራጎት ድርጅት መስራች የክብር ዶ/ር ቢኒያም በለጠ ተገኝተው ስልጠናውን ሰጥተዋል። ለሃገራችን ዋስትና እና የጀርባ አጥንት የሆነውን ገቢ በመሰብሰብ ተኪ የሌለው ሚና እየተወጡ መሆኑን ለሰልጣኞቹ በማውሳት፥ ታክስ ከፋዩን በማበረታታት እና ታክስን በትክክል በመሰብሰብ ለሚገባው አላማ እንዲውል ማድረግ አለብን ያሉት ኡስታዝ ካሚል፥ ይህ እንዲሆን ደግሞ የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራርን በህግ ብቻ ሳይሆን ራስን በመለወጥና ህሊናን ዳኛ በማድረግ መታገል ይገባል ብለዋል።

የክብር ዶ/ር ቢኒያም በለጠ በበኩላቸው፥ በገንዘብ የማይተካ መልካምነት ለትውልድ ይተርፋል በማለት ጥሩ ስነምግባር ከዋጋ በላይ እንደሆነ መናገራቸውን የገቢዎች ሚኒስቴር በፌስቡክ ገፁ አጋርቷል።

በተከታታይነት እየተሰጠ ያለው ስልጠና ለሰራተኞች የአመለካከት ለውጥ አምጥቷል ያሉት በቅ/ጽ/ቤቱ የተቋማዊ ስጋት ስራ አመራርና ስነምግባር ቡድን አስተባባሪ አቶ አማረ አለነ፥ ስልጠናው ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

# ህብረተሰቡ በፀረ-ሙስና ትግሉ እያሳየ ያለውን ተሳትፎ በማጎልበት ከተቋሙ ጋር መስራቱን እንዲቀጥል ኮሚሽኑ ጥሪ አቀረበ

ህብረተሰቡ በፀረ-ሙስና ትግሉ እያሳየ ያለውን ተሳትፎ በማጎልበት ከተቋሙ ጋር መስራቱን እንዲቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥሪ አቀረበ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር ባደረጉት ቆይታ፥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ10 ወራት በፊት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንን በማቋቋም ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን ተናግረዋል።

ከተማ አስተዳደሩ የብልሹ አሰራርና ሌብነት ለመከላከል ባቋቋመው የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ብቻ ሳይገደብ መመሪያና ደንቦችን በማዘጋጀትና በማውረድ በግብረ-ሃይል በኩል ወደ ስራ ገብቶ ውጤታማ ስራዎችን ማከናወኑንም ነው የገለጹት።

በዚህም ባለፉት 10 ወራት ከህብረተሰቡ በተሰጠ 1 ሺህ 7 መቶ በላይ የሙስናና ብልሹ አሰራር ጥቆማ፥ ምርመራን በማጠናቀር 65 በሚደርሱት ላይ ርምጃ እንዲወሰድ መደረጉን አስታውቀዋል።

በተሰጡ ጥቆማዎች መሰረት ብልሹ አሰራር የተስተዋለባቸው በርካታ ተቋማት መኖራቸውን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፥ ከጅምሩ በዚህ ደረጃ እርምጃ መወሰዱ በርካታ ሃብትን ከብክነት መከላከል እንዳስቻለም ተናግረዋል።

የፀ-ሙስና ትግልን በተቋም ደረጃ መታገል፥ ለከተማዋ





ተቋማት ግልጽነት ያለው አሰራር እንዲዘረጉ ያስችላል ያሉት ኮሚሽነር ጀማል፥ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በእኔነት ስሜት ከኮሚሽኑ ጋር አብሮ መስራት አለበት ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በአዋጅ 75/2014 ዓ.ም የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ያቋቋመ ሲሆን፥ ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ የፀረ-ሙስና ትግሉን የፌደራሉ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሲመራዉ መቆየቱ ይታወሳል።

በተያየዘ ዜና የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን "ሙስናን በመከላከል ረገድ የሚዲያና የጋዜጠኞች ሚና" በሚል መሪ ሃሳብ የኮሙንኬሽንና የሚዲያ ኃላፊዎችን የግንዛቤ ማስፈያ መድረክ አካሁዷል። በመድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወ/ሮ ቡዜና አልቃድር የብልሹ አሰራር እና የፀረ-ሙስና ትግሉ ግንባር ቀደም ሆኖ እንዲወጣ የሚዲያ አካላት ሚና የላቀ በመሆኑ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በከተማ ደረጃ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ መደረጉ የመንግስትን ቁርጠኝነት ማሳያ መሆኑን ጠቁመዋል።

ህብረተሰቡ በፀረ ... ወደ ገጽ 6 የዞረ

## ህብረተሰቡ በፀረ- ...

ከገፅ 5 የዞረ

አፈ-ጉባኤዋ አያይዘውም የብልሹ አሰራር እና የፀረ-ሙስና ትግሉ ግንባር ቀደም ሆኖ እንዲወጣ የሚዲያ አካላት ሚና ላቅ ያለ በመሆኑ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባልም ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ ከተቋቋመ በኋላ ውጤታማ ተግባራትን ከኅብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት እያከናወነ መሆኑን የተናገሩት የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፥ የሚዲያ አካላትም የተሻለ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ ስራ አስኪያጅ አቶ ካሳሁን ጎንፋ በበኩላቸው እንደ ሀገር ሙስና በመከላከል ላይ ቁርጠኝነት እንዳለ ተናግረው፥ ይህንን የሚዲያ ባለሙያዎች እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ የሚጠበቅብንን ሀላፊነት ልንወጣ ይገባል ብለዋል፡፡

አያይዘውም፥ የሙሰናና ብልሹ አሰራርን በማጋለጥ

የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት በእኔነት ስሜት መስራት ይጠበቅብናል ማለታቸውን አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዘግቧል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ በበኩላቸው፥ ሚዲያው በፀረ-ሙስና ትግሉ ማህበረሰቡን በማንቃት እና አጀንዳ በመቅረጽ የበኩሉን እንዲወጣ የመወያያ ሰነዱን ባቀረቡበት ወቅት ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽኑ በዚሁ ወር ከአዲሰ አበባ ከተማ ከተወጣጡ ከ450 በላይ ወጣቶች ጋር ሙስናን መከላለከል ላይ ዉይይት አካሂዷል፡፡ በመድረኩ መልዕክት ያስተላለፉት የአዲስ አበባ ከተማ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ ሙስናና ብልሹ አሰራር የሚቀረፈዉ በተቀናጀ አግባብ ሁሉንም ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ ቢሆንም ወጣቶች ግንባር ቀደም ሚና መጫዎት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡ አቶ ጀማል አያይዘዉም፥ ወጣትነት የአፍላ ጊዜ በመሆኑ ከወጣቶች የሚጠበቅ ግብረ ገብነትን አስጠብቆ መሄድ አስፈላጊ በመሆኑ ከወጣቶች ጋር መስራት ቅድሚያ ተሰጥቶ የሚሰራበት ነዉ ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን በበኩላቸዉ መንግስት የወጣቱን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ግልፅ አቅጣጫ አስቀምጦ እየሰራ እንደሆነ አስታዉሰዉ፥ ወጣቶች በተደራጀ አግባብ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በማደራጀት ሙስናን ሊታገሉ ይገባል ብለዋል፡፡ በመድረኩ የመወያያ ሰነዱን ያቀረቡት ምክትል ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ ወጣቶች ግብረገባዊ ግዴታቸዉን መወጣት ሲችሉ የራሳቸዉን ህይዎት በሚፈልጉት ደረጃ መምራት ከመቻላቸዉ በላይ የፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ አዎንታዊ ተሳትፎ በማድረግ የሀገር ባለዉለታ መሆን ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

በተለይም የግል ግንዛቤን በማሳደግ በስነምግባር ግንባታ፣ ትክክለኛ መረጃ በመያዝና ሙስናን በመታገል የህዝብ ወገንተኛነትን በማሳየት የራሳቸዉን አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚገባቸዉ ተገልጿል፡፡

## የደቡብ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ330 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግስትና የህዝብ ሃብት ማዳን መቻሉን አስታወቀ

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ሙስናን ለመከላከል በተሰራ ስራ ከ330 ሚሊዮን ብር በላይ የተመዘበረና ሊመዘበር የነበረ ሃብት ማዳን መቻሉን የደቡብ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮምሽኑ ምክትል ኮሚሽነርና የስነምግባር አውታሮች ማስተባበሪያ ዘርፍ ሃላፊ አቶ አማኑኤል አብደላ ለኢዜአ እንደገለጹት፥ ኮሚሽኑ የተጀመረውን እድገትና ልማት ለማስቀጠል ሙስናን አስቀድሞ መከላከል ላይ በትኩረት እየሰራ ነው፡፡



በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በህገ-ወጥ ምደባ፣ ቅጥርና ደረጃ እድገት አሰጣጥ፣ ደመወዝና እርከን ጭማሪ፣ በጨረታ አወጣጥ፣ ከህብረተሰቡ የተሰበሰበ ገንዘብ ገቢ ያላግባብ ለግለሰቦች ጥቅም ማዋልና የከተማና የገጠር መሬት ወረራ ጋር የተያያዙ 79 ጥቆማዎች ለኮሚሽኑ መቅረቡን ገልጸዋል፡፡ የደረሱ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ በተከናወኑ የቅድመ መከላከል፣ ኦዲት ግኝትና መሰል ተግባራት የተመዘበረና ሊመዘበር የነበረ ከ330 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግስትና የህዝብ ሃብት ማዳን መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ውስጥ ከ13 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆነው ገንዘብ አስቸኳይ መከላከል ስራ በመስራት ከምዝበራ ማዳን መቻሉን ጠቅሰዋል፡፡ እንዲሁም ከ16 ሚሊዮን ብር በላይ የተመዘበረ ገንዘብ ተመላሽ መደረጉን አመልክተዋል፡፡ ከዘጠኝ ወሩ የኦዲት ግኝትም ከ302 ሚሊዮን ብር በላይ የህዝብና የመንግስት ሃብት ማዳንና ማስመለስ መቻሉን ተናግረዋል፡፡ እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ገለጻ በሃሰተኛ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ የደረጃ እድገት ያገኙ ሰራተኞች ከደረጃቸው ዝቅ እንዲደረጉ በማድረግ ከ530 ሺህ ብር በላይ ማዳን ተችሏል፡፡

በገጠር ከ194 ሄክታር በላይ መሬት ማዳን መቻሉንና 24 ሄክታር የከተማ መሬት ደግሞ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ሀብትን ከማስመለስ ባሻገር በተለያዩ ደረጃ ከጉዳዩ ጋር እጃቸው ያለባቸው ከ200 በላይ ባለሙያና አመራር የሆኑ ግለሰቦችን በህግ ተጠያቂ ለማድረግ ስራዎች መሰራታቸውን አብራርተዋል፡፡

በዘጠኝ ወራት በተሰራው ስራ በየተቋማቱ ያሉ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመው "ህዝቡ ሙስናን ለመዋጋት እያሳየ ያለው ትጋትም የሚደነቅ ነው" ብለዋል፡፡

ሌብነትና ብልሹ አሰራር የክልሉን ሁለንተናዊ እድገት የሚገታ እኩይ ተግባር በመሆኑ ኮሚሽኑ በትኩረት እንደሚሰራ ተናግዋል፡፡ ህብረተሰቡ የተጀመረውን የፀረ-ሙስና ትግል ከግብ ለማድረስ በሂደቱ ላይ እያደረገ ያለውን ተሳትፎ አጠናክሮ እንዲቀጥል ኃላፊዎች ጠይቀዋል፡፡



## የቀድሞው የፈረንሳይ ፕሬዝዳንት ኒኮላስ ሳርኮዚ የቁም እስረኛ እንዲሆኑ ተወሰነ

ሳርኮዜ በ2021 የተላለፈባቸውን የሶስት አመት እስራት (ሁለት አመቱ በሌላ ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ የሚፈጸም) ቅጣት ተላልፎባቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ከምርጫ ቅስቀሳ ጋር በተያያዘ የቀረበባቸውን ክስ ከያዙ ዳኛ ጋር ያልተገባ ግንኙነት ለመፍጠርና በጉቦ ለመደለል ሞክረዋል በሚል ነበር ቅጣቱ የተላለፈባቸው፥ ሳርኮዚ ይግባኝ ጠይቀው የነበረ ሲሆን፥ የአንድ አመት እስራቱ በቤታቸው (በቁም እስር) ተፈጻሚ እንዲሆን የፈረንሳይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ወስኗል፡፡

የ68 አመቱ ሳርኮዚ ለሶስት አመታትም ህዝብ በተሰበሰበባቸው ቦታዎች እንዳይገኙ ፍርድቤቱ መወሰኑን ፍራንስ 24ን ዋቢ በማድረግ አል አይን አማረኛ ዘግቧል፡፡ የቀድሞው ፕሬዝዳንት በ2007ቱ ምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ከሊቢያው የቀድሞ መሪ ሙአመር ጋዳፊ ተቀብለውታል በተባለ ገንዘብም ክስ ሊመሰረትባቸው እንደሚችል ተነግሯል፡፡ ኒኮላስ ሳርኮዚ ከፈረንጆቹ 2007 እስከ 2012 ድረስ ፈረንሳይን መምራታቸው ይታወሳል፡፡

ብሔራዊ የሙስና ድርጊቶች ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች
ስልክ፡ 9555
አጭር የፅሁፍ መልዕክት፡ 9555
ድረ ገፅ፡ http://www.9555pmo.et/
ኢሜይል፡ http://9555pmo.et/
ቴሌግራም፡https://t.me/PMOfeedback

የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን በጥቆማ መስጫ አድራሻዎች ያጋልጡ፣ይጠቁሙ!!

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ርዕሰ -አንቀፅ

## የዲጂታል የጥቆማ ስርዓት ለፀረ-ሙስና ትግል ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው!

ሙስና ውስብስብ አለም አቀፍ ወንጀል መሆኑ የሚታወቅ ነው። ይህን አለም አቀፍ ውስበስብ ወንጀል በተለመደው የፀረ-ሙስና ትግል ብቻ መቀነስ አለመቻሉን ሀገራችን ከገባችበት ችግር መረዳት አያዳግተም። በመሆኑም ተለዋዋጭ ከሆነው አለም አብሮ በፍጥነት የሚለዋወጥ ውጤታማ የሙስና መከላከል ስልት መጠቀም ያስፈልጋል። ከነዚህ ስልቶች መካከል ደግሞ ዲጂታል የጥቆማ ስርዓት ቀዳሚው ነው።

ዜጎች የሚያጋጥማቸውን የሙስና ድርጊት በተቋማት በአካል ቀርበው ለመጠቆም ስጋት ሊያድርባቸው ይችላል። ከዚሁም በተጨማሪ ጥቆማው በትክክል ለበላይ አመራሮች ተደራሽ መደረጉን እንዲሁም ተገቢው ምርመራ ስለመደረጉ ጥርጣሬ ሊያድርባቸው እንደሚችል ይገመታል። ጥቆማዎችን በአካል ማቅረብ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ለመስጠት አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር ቢሆንም በዚያው ልክ የሰነዶች መጥፋት እና መበላሸት ከማጋጠሙም በላይ በርካታ ወጪ እና ጊዜ የሚጠይቅ ነው። ከዚያም ባለፈ ተገልጋዮች በቀጠሮ መብዛት ሊንገላቱ ይችላሉ። ከዚህ አንጻር የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር ለአጠቃቀም ምቹ የሆነ በቀላሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ጥቆማ ለማቅረብ የሚያስችል የዲጂታል ጥቆማ ስርዓት (የህዝብ አስተያት መቀበያ ስርዓት- pu-pilec feedback system) ተግባራዊ አድርጓል።

የጥቆማ ስርዓቱ በሀገር በቀል እውቀት የበለፀገ መሆኑና የደህንነት ስጋት የሌለበት ከመሆኑም በላይ በየጊዜው የሚሰጡ አስተያየቶችን መሰረት በማድረግ በቀላሉ የማሻሻል ስራዎችን ለማከናወን ጠቀሜታው የጎላ ነው። ሲስተሙ በቀጥታ በኮሚሽነሩ ክትትል የሚደረግበት መሆኑ ደግሞ መረጃዎች ሳይነጠባጠቡ በቀጥታ ተደራሽ እንዲሆን ያግዛል። በተጨማሪም የጥቆማ መረጃዎችን በጽሁፍ በምስል እና በተንቀሳቃሽ ምስል ለማቅረብ አመቺ በመሆኑ በቂ መረጃ ከማስረጃ ጋር እንዲቀርብ ያስችላል።

ዜጎች ከሀገር ውጭ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ፣ ገጠርም ሆነ ከተማ የእድሜ እና የፆታ ልዩነት ሳይኖርና የቦታ ርቀት ሳይገድባቸው ባሉበት ሆነው የእጅ ስልካቸውን ተጠቅመው የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚጠቁሙበት፣ ሙሰኛ አመራሮችን ያለ ስጋት የሚያጋልጡበት በመሆኑ ይበልጥ ተመራጭ ያደርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ተቋሚዎች የሚያጠፉትን ጊዜ እና ጉልበት እንዲሁም ገንዘብ የሚያቀል በመሆኑ በቀጣይ አይነተኛ የጥቆማ አማራጭ እንደሚሆን ይታሰባል።

ከሁሉም በላይ የሰው ልጆች እንቅስቃሴ ከቴክኖሎጂ ጋር የተቆራኘ እየሆነ በመጣበት አለም አሰራሮችን ማዘመን እና ጥቅም ላይ ማዋል ግዴታ የሚሆንበት ዘመን በመሆኑ ሲስተሙም ወደ ፊት ለዜጎች ተመራጭ የሙስና ጥቆማ ማቅረቢያ እንደሚሆን ይታመናል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም የጥቆማ ስርዓቱን ይበልጥ በማሻሻል፤ ለዜጎች የማስተዋወቅ እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን፥ ማህበረሰቡ በበለፀገው ዲጂታል የጥቆማ ስርዓት /https://epfs.gov.et/ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመጠቀም ለፀረ-ሙስና ትግሉ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪውን ያስተላልፋል።

# ቆይታ



# ሀብት ማስመዝገብ ያለበት የመንግስት አመራርና ሰራተኛ ብቻ ሳይሆን ከ18 አመት በላይ የሆነው ማንኛውም ዜጋ መሆን አለበት ፡-

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ የአስራ አንደኛ ዕትም እንግዳችን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ ናቸው፡፡ ተቋሙ በተያዘው በጀት አመት የተቋቋመ ሲሆን፥ የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ ከክቡር ጀማል ረዲ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዛ ቀርባለች፡፡ መልካም የንባብ ጊዜ...

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ኮሚሽኑ በተያዘው የ2015 በጀት አመት መቋቋሙ ይታወሳል፡፡ ከተቋቋመ ጀምሮ ምን ምን ተግባራትን አከናወነ?**

**ክቡር ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባለፈው ሀምሌ ወር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ 75/14 የተቋቋመ ሲሆን፥ ከዚያን ግዜ ጀምሮ ሃላፊዎችን የመመደብ፣ የተቋሙን ተልዕኮ መሬት ለማውረድ የሚያስችል የመዋቅር አደረጃጀት ጥናት በማጥናት የሰው ሃይል እና የደሞዝ ጥናት ነበር ያካሄደው፡፡ ይህን በመመስረት ሂደት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት ያሉ አመራሮችና ባለሞያዎች፣ የአዲስ አበባ ምክርቤት አመራሮች፣ የአዲስ አበባ ፐፐሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት አመራሮችና ባለሙያዎችና ሌሎችም በስነምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል የሚሰሩ አግዘውናል፡፡

በሂደቱም የመዋቅር አደረጃጀት ጥናቱን የሰው ኃይሉን እና የደሞዝ እስኬሉን በሚመለከተው አካላት አፀድቀን ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ስራ ከጀምርንበት ጊዜ ጀምሮ አዋጁ ላይ እንደተቀመጠው በፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም የተዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎችን እንደ ግብዓት በመውሰድ በኮሚቴ አማካኝነት ወደመከለስ ነው የተገባው፡፡ ወደ ክለሳ ስንገባ መመሪያዎች ይዘታቸውን ሳይለቁ 4 ደቦችን አዘጋጅተን በምክር ቤት አፀድቀናል፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ የሰው ኃይል ምደባ ደንብ ሲሆን፥ ደንቡን ተከትለን የሰው ኃይል የማሟላት ትግባር አከናውነናል፡፡ እንዲሁም የፌደራሉን መመሪያዎች በማየት የተለያዩ 8 መመሪያዎች አዘጋጅተን በማጽደቅ በፍትህ ሚኒስቴር እንዲመዘገቡ ተልከዋል፡፡ እነዚህን ተግባራት በማከናወን ስራውን ጀምረናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስራዎችን ጀምረን የሰው ኃይል ወደ ማሟላት፣ ቢሮ ወደ መከራየት፣ በጀት ማስመደብ፣ ተሽከርካሪ መግዛት፣ የውስጥ ወንበሮች፣ ላብቶፖች፣ ኮፒተሮች የሟሟት ስራ ነው፤ አሁን ባለበት ደረጃ ከሃላፊዎች ውጭ 28 ሰራተኞችን አሟልተናል፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ኮሚሽኑ ነፃና ገልተኝነት እንዴት ይታያል? የከተማ አስተዳደር አመራሩ ድጋፍስ እንዴት ይገለፃል?**

**ክቡር ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፡-** ከተማ አስተዳደሩ የተቋሙን ነጻነት ለመጠበቅ ያለው ቁርጠኝነት በጣም ደስ ይላል፡፡ በርግጥ መጀመሪያውንም የፀረ-ሙስና ትግሉ በተቋም እንዲሆን ካለው ቁርጠኝነት የተነሳ ተቋሙን ያደራጀው፤ እኛም ከዚህ ከመጣን በኃላ ከተማ አስተዳደሩ የነበረውን የስራ ቁርጠኝነት በተግባር ያሳየ ነው፡፡ በተለይ ቢሮ በመፈለግ፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በሟሟላት፣ ተሽከርካሪን ጨምሮ የሰው ኃይልን በመመደብ በርካታ እገዛዎችን እያደረግን ነው ያለነው፡፡ እገዛ ስንል ከንቲባ ፅ/ቤት ብቻ አይደልም፡፡ ከዚህም ባለፈ ምክር ቤቱም ቢሆን ትልቅ እገዛ ያደርግልናል፤ ሌሎችም ተቋማት ባለሞያዎቻቸውን አመራሮቻቸውን፣ ፍትህ ቢሮም በተመሳሳይ ባለሞያዎቻቸውን እና አመራሮቻቸውን በመመደብ እገዛ እያደረጉልን ነው፡፡ አሁን ባለንበት ደረጃ ወደ




አደረጃጀቱ ስራ ገብተናል ማለትት ነው፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ባለፋት ጥቂት ጊዜያት ከተለያዩ አካላት ጋር ማለትም የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የሚዲያ ተወካዮች፣ የወጣት አደረጃጀቶች ጋር መድረኮችን ማካሄድ ችላችኋል፡፡ የተሳታፊዎችን ስሜት እንዴት አገኛችሁት? በቀጣይስ ምን ታስቧል?**

**ክቡር ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፡-** በዚህ ሰሞን በተለያዩ ሚዲያዎች የሙስና ተግባር ምጩ የአስተሳሰብ ችግር ነው፤ የአስተሳሰብ ችግር ነው ስንል ሰው አስተሳሰቡ ሲቆሸሽና ሲበላሽ ነው፡፡ የህዝቡንና የመንግስትን ሀብት ለመዝረፍ፣ ከመዝረፍም ካለፈ በአደባባይ ሲጠቀሙበት የምናየው ማለት ነው፤ ይሄ እንግዲህ በማጥናት፣ በመመርመርና በመክሰስ በህግ በማስቀጣት ብቻ ችግሩን ልንሻገር እንደማንችል ተገንዝበን ሌሎች ሰፊ መድረኮችን ማለትም ከማህበረሰብ አንቂዎችን፣ ከሚዲያ አካላት፣ ከጋዜጠኞች፣ ከመምህራንና ከትምህር አመራር አካላት እንዲሁም የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመን በክበባትና በሌሎች ተግባርት አብረን ለመስራት ችለናል፡፡ በቀጣይ ከ900 በላይ የሃይማኖት አባቶች የሚሳተፉበት ትልቅ መድረክ አዘጋጅተናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሚዲያዎች በመድረኩ ተገኝተው ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲያደርጉ እንጋብዛልን፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ግዙፍ ኢኮኖሚ የሚያንቀሳቅስ በመሆኑ አገልግሎት አሰጣጡን ከብልሹ አሰራር ስመከላከል ምን ስመስራት ታስቧል?**

**ክቡር ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፡-** በሌሎች ከተሞች የኢዱስትሪ እና የፖለቲካ ከተማ እንዲሁም የቱሪዝም መዓከል ከተማ ሲኖር፥ በእኛ ሀገር ግን የኢድስትሪ፣ የፖለቲካ፣ የቱሪስት መዓከሉም ጭምር አንድ ቦታ የተሰባሰበ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኛው የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ለውውጥ ከ70 ከመቶው በላይ አዲስ አበባ ያለ ነው፡፡

ስለሆነም የሀብት ክምችቱ ከዚሁ ከተማ ነው ያለ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በዘላቂነት የማህበረሰቡን

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካሉት 11 ክፍለ ከተሞች የ10 ክፍለ ከተማ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደራጀተን ጨርሰናል**

አስተሳሰብ በመቅረፅ ነባር የማህበረሰቡን ልምዶች እንዲያሰራሩና ህብረተሰቡ ሌብነትን እና ሙስናን እንዲጠየፍ፣ ትውልዱ እንዲገነባ ከምናደርገው ስራ በሌላ በኩል የሀብት ማስመለስ ስራ መስራት አለብን፡፡

እኛ እያሰብን ያለነው ሀብት መመዝገብ ያለበት የመንግስት አመርርና ባለሙያ ብቻ አይደለም፡፡ እድሜው 18 አመት የሞላው በሙሉ ሀብቱን ማስመዝገብ አለበት የሚል አቋም አለን፡፡ ስለዚህ ሀብቱ የሚመዘገብ ከሆነ ሌብነትን መቀነስ እንችላለን፡፡ ምክኒያቱም እንደምናውቀው እኛ በጓደኝነት፣ በቤተሰብ፣ በብሄር የተሳሰረ ማህበረሰብ ነው ያለው፡፡ ሀብቱን በሚስቱ፣ በልጁ፣ በቤተሰቡ፣ እና በጓደኛው ጭምር ነው የሚያስቀምጠው፡፡ ይህን ለማስቀረት መንግስት አሰራሮችን በቴክኖሎጂ የተደገፈ እያደረገ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አዲስ አበባ ያለውን ችግር መቀነስ ይቻላል ብለን እናስባለን፡፡ የፀረ-ሙስና ትግሉ በከተማና በገጠር እየተጠናከረ ሊሄድ ስለሚችል አንዱ መንገድ የስነምግባር ግንባታው እንደተጠበቀ ሁኖ ሀብት ማስመዝገቡ በተወሰነ ክፍል የታጠረ ሳይሆን ሁሉም እድሜው ለአቅመ አድምና ሄዋን የደረሰ ሀብት እንዲያስመዘግብ ለማድረግ ሲስተም እያበለፀግን ነው፡፡

**የ€€ፀረ-ሙስና« ጋዜጣ፡- የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን ስማደራጀት እና ስመደገፍ ያስው ዝግጅት እንዴት ይገለፃል?**

**ክቡር ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፡-** የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ለፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽ ተጠሪ በነበሩበት ጊዜ የነበሩትን በስነምግባራቸው በመለየት እየመደብን እንገኛለን፡፡ የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአዲስ አበባ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በሚከታተልበት ጊዜ የነበሩ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጥሩ የሚሰሩ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንደመኖራቸው ስራቸውን በአግባቡ የማይሰሩ ባለሞያዎችም አሉ፡፡ በመሆኑም ማደራጀት የጀመርነው አዲስ አበባ ከ120 በላይ ወረዳ 11 ክ/ከተማ በከተማው በቢሮዎችና በተቋማት ሁሉንም ስለማናውቃቸው ከተቋም ሃላፊዎች፣ ከቢሮ ሃላፊዎች እና አመራሮች በተቀናጀ መንገድ የፀረ-ሙስና ትግሉ ፍሬ እንዲያፈራ ሊያታግሉ የሚችሉ ስነምግባራቸውን፣ ልምዳቸውን እና ምስጉን የሆኑ ባለሙያዎችን ወደ መመልመል ሂደት ነው የሄድነው፡፡ ስንመለምል ከነበሩት ብቻ ሳይሆን ከሌሎች አላማ ፈፃሚዎች ዳሪክተሮች በሙሉ ስነምግባራቸው የተመሰከረላቸው ብቻ እንዲመጡ ነው ያደረግነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከ11 ክፍለ ከተሞች የ10 ክ/ከተማ አደራጀተን ጨርሰናል፡፡ ወረዳዎች ላይም የተሻሉ ባለሙያዎችን በጣም አሳታፊ በሆነ መንገድ ለማደረጃት ችለናል፡፡ አሁን ለመደብናቸው የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሻለ ስልጠና በቅርቡ እንሰጣቸዋል፡፡ ስልጠናው መመሪያውና አዋጆች እንዲሁም የአሰራር ስራዓቶቹና ከሌሎች ዘርፎች ጋር እንዴት ተቀናጅተው መስራት እንዳለባቸው ግንዛቤ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ምክኒያቱም የሴክተሩ ባህሪ ከሌሎች ሴክተሮች ጋር በቅንጅት የሚሰራ ነው፡፡ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከሚዲያዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እንዴት መስራት እንዳለባቸው የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ግንዛቤ የምንፈጥርላቸው ይሆናል፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ድጋፍ እንደት አገኛችሁት?**

**ክቡር ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፡-** ብዙ ነገሮችን መነሻ ያደረግነው የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አሰራርን ነው፡፡ እንዴት ይሰራ እንደነበር መዋቅር፣ ደንቦችና ጥናት ላይ እገዛ እንዲያደርጉልን ጠይቀን ሲያግዙን የነበሩ ጠንካራ ባለሙያዎች አሉ፡፡ አመራሮችም ወደፊት የበለጠ ያግዙናል ብለን እናስባለን፡፡ በተለይ የውስጥ ቁሳቁስ በሟሟላት ረገድ የተሻለ እንዲያግዙን እንፈልጋለን፡፡

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የተቋማት የግዥ ስርዓትና ሙስና

ተስፋዬ ሻሜቦ

ተቋማት የግዥ ዕቅድ በማቀድና የትግበራ መርሃ ግብር በማዘጋጀት በወቅቱ ማከናወን ሲገባቸው ብዙውን ጊዜ የበጀት ዓመት ማጠናቀቂያ አካባቢ /ግንቦትና ሰኔ ወር/ በሩጫ ግዥ ለመፈጸም የሚያደርጉት ጥረቶች መኖራቸው ይታወቃል:: በመሆኑም ከዕቅድ ውጪ በሩጫ የሚከናወኑ የግዥ አፈፃጸሞች አብዛኛውን ጊዜ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ያለው ሥጋት ከፍተኛ ነው:: ከዚህ አንፃር የተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ሌሎች በተቋሙ የሚመለከታቸው አካላት በዘርፉ የሚፈጸሙ የሙስና ሥጋት ችግሮችን በመረዳት ለመከላከል እንዲረዳቸው ይህ ጽሑፍ ተዘጋጅቷል::

ተቋማት ከበጀት ዓመት ውስጥ ከፍተኛውን በጀት የሚመድቡት ለግዥ መሆኑ ይታወቃል:: ይህ የግዥ በጀት ጥቅም ላይ ለማዋል ቁጠባን፣ ፍትሃዊነት፣ ተጠያቂነትን፣ ግልጽነትና ቀጣይነት መርሆዎችን መከተል እንዳለብን ሳይንሱ ያስገድዳል:: በመሆኑም ለበጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት 40 እስከ 60 በመቶ በላይ ያህሉ ለዕቃ ወይም ለአገልግሎት ግዥ ይፈጽምበታል:: ግዥ የሚፈጸመው የተቋም ተልእኮን ከማሳካት አንፃር እንደሚሆንም ይገመታል:: ስለሆነም የበጀት ዓመት የበጀት ዕቅድ ሲታቀድ የደመወዝ ክፍያና ግዥ የሚፈጽምበት በጀት ይታቀዳል:: የሚታቀደው በጀት ለዕቃ ወይም ለአገልግሎት ግዥ ሊሆን ይችላል:: የበጀት ዓመት የግዥ ሲታቀድ መጀመሪያ የተፈለገው ዕቃ ወይም አገልግሎት በተቋም ግምጃ ቤት ውስጥ ወይም ውጪ ውስጥ ስለመኖሩና አስፈላጊነቱ ላይ ማረጋገጫ ይወሰዳል:: ዕቃው ደግሞ አላቂ ወይም ቋሚ ዕቃ ሊሆን ይችላል::

ለበጀት ዓመት ግዥ የሚፈጽምበት ዕቃ በተቋም ውስጥ ስለመኖሩ ለማረጋገጥ በቅድሚያ ለተቋሙ ያለው ቋሚና አላቂ ዕቃ በተገቢው መንገድ በዲጂታል አሠራር ጭምር ተመዝግቦ መያዝ ይኖርበታል:: ቋሚ ዕቃዎች ከህንፃ ጋር ተያያዥ ወይም ለሥራ ክፍሎች ለጋራ አጠቃቀም የተቀመጠ ዕቃ ካልሆነ በስተቀር በበቂ መረጃ ላይ በተደገፈ ሁኔታ በተጠቃሚ ስም ተመዝግቦ በማህደር ወይም በዲጂታል አሠራር መያዝ አለበት:: መረጃው የቋሚ ዕቃ ስም፣ ዓይነት፣ የመለያ ቁጥር፣ ከለር፣ ይዘትና የተመረተበት ሀገርና ዓመት እና የተገዛበት ዋጋ ወዘተ... በዝርዝር ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል::

አላቂ ዕቃዎች ደግሞ በግምጃ ቤት ውስጥ በሼልፍ ላይ ወይም ከሼልፍ ውጪ በተለያየ ሁኔታ ሊቀመጡ ይችላሉ:: እነዚህ እቃዎች በየጊዜው ቆጠራ እየተካሄደባቸው ለማረጋገጥ የእያንዳንዱ ዕቃ ከዕቃው ጋር የተያየዘ ቢን ካርድና ለንብረት አስተዳደር ክፍል የሚያዝ ስቶክ ካርድ ተዘጋጅቶላቸው በሥርዓቱ ተመዝግቦ መያዝ ይኖርበቸዋል::

የዕቃ ግዥ የሚባሉት ቋሚ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎች፣ ህንፃዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ ፎቶኮፒ ማሽኖች፣ ፕሪንተሮች፣ የጽህፈት መሳሪያዎች፣ የደንብ ልብሶች እና ለምግብ ዝግጅት የሚያገለግሉ ዕቃዎች ወዘተ ሲሆኑ፥ የእነዚህ ዕቃዎች አስፈላጊነታቸውና አዋጭነታቸውን በሚገባ በዳሰሳ ጥናት ጭምር ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተለይ በግምጃ ቤት ውስጥ የሚቀመጡ ዕቃዎችን ላይ ቆጠራ በማካሄድ ያለው መጠን ከታወቀ በኋላ የሚያስፈልገው መጠን ብቻ መገዛት አለበት::

የአገልግሎት ግዥ ለምሳሌ፡- የጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ የሆቴል አገልግሎቶች፣ የጥገና ሥራዎች፣ የሚዲያ ግዥዎች ወዘተ የመሳሰሉት የአገልግሎት ግዥዎች በቅድሚያ የሥራ አስፈላጊነትና አዋጭነት ላይ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀትን ይጠይቃል:: እነዚህ ሥራዎች በቀላሉ ለሌብነት ተጋላጭ ሊሆኑ ስለሚችሉ፥ የሚፈጸሙ የአገልግሎት ግዥዎች ዕቅድ ተይዞላቸው በተቋም የበላይ ኃላፊዎች ዕውቅና የተሰጣቸው ሊሆኑ ይገባል::

የተቋም የበጀት ዓመት የዕቃ የግዥ ዕቅድ ሲያዝ፥



ተቋሙ ያለው ቋሚና አላቂ ዕቃ በቆጠራ ሪፖርት ተመስርቶ መረጃ መያዝ አለበት:: የሥራ ክፍል ውስጥ ዕቃ ወይም አገልግሎት ፈላጊ የሆኑ ሥራ ክፍሎች ጥያቄያቸውን በዓይነት፣ በመጠንና በዋጋ ለይተው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ መደረግ ይኖርበታል::

ከሥራ ክፍሎች በቀረበው መረጃ መሠረት ተመሳሳይ ዕቃዎችን በአንድ ላይ በማደረጃት የዕቃ ግዥ ወይም የአገልግሎት ግዥ ዕቅድ ማዘጋጀትና ለተቋሙ ማኔጅመንት በማቅረብ ማፅደቅ ያስፈልጋል::

የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ዕቅድ በበጀት ሊደገፍ ስለሚገባ፥ የታቀደውን የግዥ ዕቅድ ከተፈቀደው በጀት ጋር በማመሳከር ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከዚህ በመነሳት የፀደቀው የግዥ ዕቅድ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የግዥ ፍላጎት ካቀረበው የሥራ ክፍል መረጃ ላይ ተመስርቶ የግዥ አፈፃፀም የትግበራ መርሃ ግብር ማዘጋጀት ያስፈልጋል::

በትግበራ መርሃ ግብሩ ላይ ግዥ የሚፈጸምበት ጊዜና መጠን በተጨማሪ የጨረታ ግዥ ዘዴዎችን በመለየትና በመወሰን መታቀድ ይኖርበታል:: በታቀደው ግዥ ላይ በተቋሙ የበላይ አመራር ወሳኝ ሚናና የሚመለከታተቸው የስራ ክፍሎች የማረጋገጥ ተሳትፎ በበቂ ሁኔታ ማካተት የግድ ነው:: የሥራ ክፍሎች ተሳትፏቸውን የሚገልፁት የተዘጋጁ የግዥ ዕቅድ ሰነዶች ተልኮላቸዋው አስተያየት በመስጠት ወይም የግምገማ መድረክ በማዘጋጀትና ገለፃ ተደርጎላቸው መሆን አለበት::

የታቀደው ግዥ ለመፈጸም ይህን ሥራ በመከታተልና በመገምገም ትክክለኛነትን በማረጋገጥ ዕውቅና የሚሰጥ የግዥ ጨረታ ኮሚቴ ማዋቀርም የግድ ይላል:: የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀደም ሲል የታቀደው ግዥ በጨረታ እንዲፈጸም መከታተልና ማረጋገጥ ይገባቸዋል:: የጨረታ ግዥ ሲፈጸም የሚያገጥሙ ችግሮች ለጨረታ ኮሚቴ እየቀረበ ዕውቅና ሲሰጥ ብቻ ሌላ አማራጭ የግዥ ዘዴ ተግባራዊ መሆን አለበት::

የግዥ ኡደት አራት ሲሆኑ፥ የግዥ ዕቅድ ዝግጅት፣ ሰነድ ዝግጅት፣ ግዥ ግምገማና የውል አስተዳደር የሚሉት ናቸው:: በኡደት ላይ ሙስና ለመስራት ዝግጅት የሚጠነሰሰውና የሚታሰበው የግዥ ፍላጎት ስብስባና ዕቅድ ሲታቀድ ነው:: በሙስና ለመክበር የሚፈልጉ የሥራ ክፍል ኃላፊና ሠራተኞች ለሥራ ክፍል ሥራ ጠቃሜታ የማይሰጠውን ወይም ታቅዶ ከሚከናወነው ሥራ አቅም በላይ የሆነ የግዥ ፍላጎት ጥያቄ ያቀርባሉ:: በተለይ የማያስፈልጉ ዕቃዎች ግዥ ይፈጸምና ዕቃዎች ለፀሐይና ዝናብ እንዲጋለጡ የሚደረገው ከዚህ አንፃር እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል:: ይህን ተገቢነት የሌለውንና የተጭበረበረውን የግዥ ፍላጎት የሚሰበሰብ የሥራ ክፍልም ከፍላጎት አቅራቢ የሥራ ክፍል ጋር በመመሳጠር በሚፈጽሙት ደባ/ተንኮል የተሰበሰበው የግዥ ፍላጎት መረጃዎች ከገበያ በሚያገኘው ዋጋ ጋር ማመሳከርና ማጣራት ሳይሠራ በቀጥታ ወደ ግዥ መፈጸም ስለሚሄዱ እንዲሁም የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት አስፈላጊነትና አዋጭነት በትክክል ሳይረጋገጥ የሚወሰደው እርምጃ በቀጥታ ሙስና ለመሥራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ማለት ነው::

ስለሆነም እያንዳንዱ የግዥ ዘዴ ላይ የሚፈጸም ሙስና በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ነው::

የመጀመሪያ የግልጽ ጨረታ ዘዴን እንመለከት:: ሁሉም ተቋማት የተለየ ሁኔታ ወይም ችግር ካለጋጠማቸው በስተቀር የግልጽ ጨረታ ዘዴን በመጠቀም ግዥ እንዲፈጽሙ በህግ ይገዳደሉ:: ግዥ ታቅዶ፣ ለታቀደው ግዥ ዝርዝር መግለጫ ተዘጋጅቶለት፣ የገቢያ ዋጋ ጥናት በማካሄድ እንዲሁም የግልፅ ጨረታ መመሪያና የተጫራች ማወዳደሪያ የመመዘኛ መሥፈርት በማዘጋጀት በግልጽ ተደራሽ በሚሆን ሚዲያዎች ላይ ይወጣል::

የወጣው የጨረታው ማስታወቂያ በመመሪያው መሠረት አየር ላይ ይቆያል:: የጨረታ ማስታወቂያ ከተከፈተ በኋላ በጨረታ ኮሚቴ ዕውቅና ለቴክኒክ ግምገማ መላክ አለበት:: ቴክኒክ ግምገማ መካሄድ ያለበት በግዥ ዕቅድ እስከ ጨረታ ማውጣት ድረስ በሚከናወኑ ሥራዎች ላይ ሚና የሌላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው:: በአጠቃላይ ነፃና ገለልተኛ በሆኑ ሰዎች የቴክኒክ ግምገማ ሊካሄድ ይገባል::

የአቅራቢዎች የቴክኒክ ግምገማ ላይ የሚሳተፉት ቀደም ሲል የግዥ ፍላጎት ያቀረበው የሥራ ክፍል ሰው ሊሆን አይገበም:: የቴክኒክ ግምገማ የመመዘኛ መስፈርቱም ቀደም ሲል ጨረታው ሲወጣ በተዘጋጀው የመመዘኛ መሥፈርት እንጅ ሌላ አዲስ በማዘጋጀት ሊሆን አይገበም::

በተቋማት ሁሉም ግዥዎች በግልጽ ጨረታ ለመግዛት ቅድሚያ እንዲሰጥ የሀገሪቱ የግዥ ህግ ያዛል:: ነገር ግን የግልፅ ጨረታ ዘዴን በመጠቀም ለመግዛት የማይፈቅዱ ሁኔታዎች ሲገጥሙ ሌሎች ዘዴዎች መጠቀምን መመሪያው ይፈቅዳል::

ሆኖም ግን ሁሉም ዘዴዎች ላይ የሙስና ችግር ይከሰታል:: በግልጽ ጨረታ ዘዴ ላይ የሙስና ችግር የሚጀምረው ወይም የሚጠነሰሰው ከዕቅድ ጀምሮ ነው:: መጀመሪያ ለተቋሙ የማይጠቅም ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ዕቅድ ይታቀዳል:: ለግዥ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ተደርጎ ይታቀደል:: አቅራቢ ድርጅት ግዥ የሚፈጽምበትን የእቃና አገልግሎት ግዥ ዝርዝር መግለጫ አዘጋጅቶ ያቀርብና ጨረታው ሲወጣ አሸናፊ እንዲሆን ይደረጋል:: የሚወጠው ግልጽ ጨረታ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ለአቅራቢ በአግባቡ ተደራሽ አይደረግም:: ለሚፈጸም ግዥ የገበያ ዋጋ ግምት አይያዝም::

ቀደም ሲል ዝርዝር መግለጫ ያዘጋጀው አቅራቢ በተጋነነ ዋጋ ተወዳድሮ እንዲያሸንፍ ይደረጋል:: ጨረታው የሚከፈትበት ቀን እንዲያጥር ይደረጋል፥ አቅራቢ ሳይገኝ ጨረታ ይከፈታል:: የሚፈልግ አቅራቢ የመመዘኛ መስፈርት እንኳን ሳያሟለ የጨረታው ተወዳዳሪና አሸናፊ እንዲሆን ይደረጋል::

ጨረታው ከተከፈተ በኋላ በአፈጣኝ የቴክኒክ ግምገማ አይፈጸምም፥ በቆይታ ጉቦ የሚሰጥ አቅራቢ ይፈለጋል:: አቅራቢዎች ያቀረቡት መረጃ ከታየ በኃላ የሚፈለግ አቅራቢ እንዲያሸንፍ የመመዘኛ መስፈርት ተከልሶ ይዘጋጃል:: የአንዱ አቅራቢ መረጃ በረቀቀ ዘዴ ለሌኛውና እንዲያሸንፍ ለሚፈለግ ተወዳደሪ አቅራቢ ሊሰጥ ይችላል:: ቀደም ሲል ለአቅራቢ ግልጽ ባልተደረገ የመመዝኛ መስፈርት የቴክኒክ ግምገማ ይፈጸማል:: ለጨረታ ውድድር በቂ መስፈርት ያላሟላ አቅራቢ እንዲወዳደር ይፈቃዳል:: የቴክኒክ ግምገማ ያላለፈ አቅራቢ የፋይናንስ ግምገማ እንዲያልፍ ይፈቀዳል:: የጨረታ ኮሚቴዎች ሳይሟሉ አሸናፊ አቅራቢ እንዲለይ ይደረጋል፥ ዝቅተኛ የቴክኒክ ግምገማ ውጤት ያስመዘገበ አቅራቢ ከፍተኛ የፋይናንስ ዋጋ በማቅረብ እንዲያሸንፍ ይፈቃዳል:: በጨረታ ኮሚቴ ውስጥ የአቅራቢ ዘመድ ስለሚኖር የጨረታ ውሳኔውን ለዘመዱ ሊያመቻች ይችላል::

የውስን ጨረታ ዘዴ ሁለተኛው ዘዴ ሲሆን፥ ይህ ዘዴ የግልጽ ጨረታ ዘዴ በተደጋጋሚ በማውጣት ግዥ መፈጸም ካልታቻለ ለጥቅም የሚውል ነው:: ስለሆነም የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር መግለጫዎችና የግምገማ መመዘኛ መሥፈርቶችን ከግዥ መመሪያ ጋር በማዘጋጀት ከአምስት ላላነሱ አቅራቢዎች በመላክ በሚሰጡት መረጃና ዋጋ በማወዳደርና በመረጃ ግምገማ የተሻለ ውጤት ያመጠውንና ዝቅተኛ ዋጋ የሠጠውን አቅራቢ በመጋበዝ የሚፈጸም ነው:: በዚህ ዘዴ አጠቃቀም ላይ በቅድሚያ የግልጽ ጨረታ ዘዴ ለመጠቀም ሳይሞከርና በጊዜ የለንም ሰበብ ዝርዝር መግለጫ የተፈለገው አቅራቢ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ማድረግ፣ የአንዱን አቅራቢ መረጃ ለሌላው በመስጠት የሚፈለገው አቅራቢ እንዲያሸንፍ ማድረግ፣ አንድ አቅራቢ ድርጅት የአምስት አቅራቢዎችን መረጃ በማደራጀትና ራሱ እንደሚያሸንፍ በማድረግ በሚያቀርበው ዋጋ መሠረት እንዲያሸንፍ መፍቀድ እና አንድ ጉቦ ለመስጠት ያቀደ አቅራቢ እንዲያሸንፍ የተመቻቸ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛ መሥፈርት ማዘጋጀት ወዘተ በመሥራት ሙስና ይሠራበታል::

የዋጋ ማወዳደሪያ የሚፈፀም ግዥ ሦስተኛው የግዥ ዘዴ ሲሆን፥ ይህ ግዥዎችን በዕቅድ በማከፋፋልና በማበጣጠስ ያለ ዕቅድ ወይም በዕቅድ የሚፈጸም ግዥ ነው:: በተለይም በዚህ የግዥ ፍላጎቶችን በመሰብሰብና በዓይነት በመለየት በዕቅድ ከመግዛት ይልቅ በማከፋፋል የሚፈጸም ግዥ ሲሆን፥ በዚህ ግዥ ዘዴ ከአንድ አቅራቢ ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ በተጋነነ ዋጋ ግዥ በመፈፀም ወይም አንድ አቅራቢ ሦስቱንም የዋጋ ማወዳደሪያዎች እንዲያዘጋጅ በመፍቀድና በተደጋጋሚ ግዥ በመፈጸም ሙስና ይፈፃማል።

ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ አራተኛው የግዥ ዘዴ ሲሆ፥ ብዙውን ጊዜ ብቸኛ የእቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ አቅራቢ ከሆነ በቀጥታ የግዥ ትዕዛዝ በመስጠት ግዥ ይፈጸማል:: ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ አንድ ብቸኛ አቅራቢ ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ሳይያዝና ከአቅራቢው ጋር በመመሳጠር በተጋነነ ዋጋ ግዥ በመፈጸም ወይም ጥራት የሌለው ዕቃ ወይም አገልግሎት በተጋነነ ዋጋ ግዥ በመፈፀም ሙስና ይሰረበታል::

በመወዳደሪያ ሀሳብ የሚፈጸም ግዥ አምስተኛው ግዥ ዘዴ ሲሆን፥ አቅራቢዎች መጀመሪያ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ተደርጎ የተሻለ ሀሳብ ያቀረበው አቅራቢ አሸናፊ የሚሆንበት ዘዴ ነው:: በዚህ ዘዴ በቅድሚያ የሚፈለገውን ሀሳብ ለተፈለገው አቅራቢ በመስጠት የጨረታ አሸናፊ እንዲሆን ሁኔታዎች በማመቻቸት ወይም የቀረበውን ሀሳብ ለማወዳደር የሚዘጋጀው የመመዘኛ መሥፈርት ከአቅራቢው ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም በማድረግና በመመዘን ሙስና ይፈጸማል::

በሁለት ደረጃ የሚፈጸም ግዥ ዘዴ ስድስተኛ ግዥ ዘዴ ሲሆን፥` ይህን ዘዴን ለመጠቀም የሚፈለገው ዕቃ ወይም አገልግሎት በተቋም ደረጃ የማይታወቅ ስለሆነ ተወዳደሪ

የተቋማት የግዥ ... ወደ ገጽ 11 የዞረ

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር



ይህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚያደረገው ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ በማስገኘት ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ወይም ለሌላ ሰው ያስገኘ ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግሰት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ ወይም ከማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላት መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የምዳረግበት ነው።

## የሙስና ወንጀል የፍርድ ሂደቶች

በሙስና ወንጀል ላይ የፌደራል ፍርድ ቤቶችንና የሁሉንም የክልል ፍርድ ቤቶችን የክርክርና የውሳኔ ሂደት አልፈው በይግባኝ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት ደርሰው ውሳኔ ያገኙ የሙስና ወንጀል ፍርድ ሂደቶች የህግ እውቀታችንና የሙስና ወንጀሎች እንዴት እንደሚፈፀሙና ወንጀሉን የፈፀሙ ሙሰኞች እንዴት ከህግ ለማምለጥ እንደሚጥሩ የፍትህ ስርዐታችንም እንዚህን ሙሰኞች የፈፀሙትን የረቀቀ የሙስና ወንጀል ተግባር በህግ ፊት አቅርቦና በተሟላ ማስረጃ አረጋግጦ የህግ የበላይነትን የማረጋገጥና ሙሰኞች የፈለገ የረቀቀ ሙስና ወንጀል ቢፈፅሙ የትም ማምለጥ እንደማይችሉ በማረጋገጥ ዙሪያ ያለውን እጅግ ፈታኝ ሁኔታና የፍትህ ስርዐታችን ዐቅም እንድናውቅ በማድረግ የበኩላችንን ድጋፍ እንድናደርግ ያግዘናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ትከተል በነበረው የሲቪል ሎው ሌጋል ሲስተም / civil law legal system / ወይም የተፃፈ ህግን / codified law / ከሚከተሉ ሀገራት አንዷ በነበረችበት ወቅት የኮመን ሎው/ common law / ወይም የኬዝ ሎው /case law / ከሚከተሉ ሀገራት የምትለይበት አንዱና ዋናው ነጥብ እንደ ኮመን ሎው ሀገራት የሀገሪቱ የበላይ የመጨረሻ ፍርድ ቤት በእነሱ ጁሪዎች / juri / ውሳኔ በእኛ ደግሞ የሀገራችን ፍርድ ቤት የመጨረሻው የዳኝነት እርከን በሆነው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት ዳኞች / judges / በሙስናና በሌሎች የወንጀልና የፍትሀብሄር ክርክር ውሳኔዎች ከስር ላሉ ሁሉም የፌደራልና የሁሉም ክልሎች ፍርድ ቤቶች ልክ እንደተፃፈና በህግ መወሰኛው ምክር ቤት ፓርላማ እንደወጣ ህግ ተደርጎ በቀጥታ እንዳይተገብሩ / presidence / የሚከለክለውን ህግ በመቀየር የሁለቱንም አይነት የህግ ሥርዐቶች / civil law and common law mixed legal system / ወደ መከተል በመምጣት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት የሚወሰኑ ማናቸውም ውሳኔዎች በማናቸውም በሀገሪቱ በሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች እንደፕሪስደንስ ተደርገው በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ በተወሰነውና እየተተገበረ ባለው በሙስና ወንጀሎች ላይ በሠበር የተወሰኑ ውሳኔዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ በሁሉም የሀገሪቱ ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ እንደሚተገበሩ እንዳሉ ለአንባቢያን እውቀትና ግንዛቤ መፍጠሩ በኮሚሽኑ ታምኖበት ከዚህ ግንቦት ወር እትም ጀምሮ በየወሩ በቋሚነት እየታተሙ ለአንባቢያን እንዲደርሱ ማድረግ አንዱና ዋናው ምክንያት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በስር የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች እንደ አስገዳጅ ህግ ሆነው በተመሳሳይ ጉዳዎች ላይ ማጣቀሻ ሆነው ተመሳሳይ ውሳኔ እንዲሰጣቸው የመደረጉ የሀገራችን ህግን ማወቁ ለአንባቢያን በሚያጋጥማቸው በየትኛውም ፍርድ ቤት በሚያጋጥማቸው ከሠበር ውሳኔ ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳዮች ውሳኔ እንዲሰጣቸው የሠበርን ውሳኔ መዝገብ ጠቅሰው ማስወሰን እንደሚችሉ ከማወቅም ባለፈ በተመሳሳይ ሁኔታ በሙስና ወንጀሎች ላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት የወሰናቸውን ውሳኔዎችን ማወቅ በየአካባቢያቸው የሚፈፀሙ የተለያዩ ሙስና ወንጀሎችን ከሠበር ውሳኔ ሂደት ጋር በማገናዘብ የየራሳቸውን ሚና በፀረ ሙስና ትግሉ እንዲያደርጉም ጭምር ያግዛል።

በዚሁ መሰረት የመጀመሪያው መረጃ ሜ/ጀኔራል ክንፈ ዳኘው በቀረበባቸው ስልጣንን ያለአግባብ የመጠቀም የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ መባላቸውን የሚያትት ነው የቀድሞ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) ዋና ዳይሬክተር ሜጀር ጀኔራል ክንፈ ዳኘው ከ11 ራዳሮች ግዢ ጋር ተያይዞ በቀረበባቸው ስልጣንን ያለአግባብ የመጠቀም የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ተብለዋል።

የጥፋተኝነት ፍርዱን ያስተላለፈው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ነው። በፍትሕ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ህዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም ላይ ጥራቱን ያልጠበቀ 11 ራዳር በ214 ሚሊየን ብር በላይ ወጪ በመግዛት በመንግስት ላይ ጉዳት ደርሷል በሚል በአራት ተከሳሾች ላይ የመንግስት ስራን በማያመች አኳኃን የመምራት ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መስርቶባቸው እንደነበር ይታወሳል።

በወቅቱ ክስ ቀርቦባቸው የነበሩት ተከሳሾቹ 1ኛ የሜቴክ ዋና ዳይሬክተር የነበሩት ሜጀር ጀኔራል ክንፈ ዳኘው፣ 2ኛ ሌተናል ኮሎኔል ፀጋዬ አንሙት፣ 3ኛ ኮሎኔል ሸጋው ሙሉጌታ እና 4ኛ የስነምግባርና የሕግ ክፍል ኃላፊ የነበሩት ኮሎኔል መሐመድ ብርሃን አብርሃ ሲሆኑ፥ ክሱ ከቀረበ በኋላ ግን የሜጀር ጀኔራል ክንፈ እና የኮሎኔል መሐመድ ብርሃን መዝገብ ብቻ ሲቀጥል የሌሎቹ ክስ በተለያዩ ምክንያቶች እንዲቋረጥ ተደርጓል።

ይህም በወቅቱ ቀርቦ የነበረው ክስ ላይ ተከሳሾቹ የብረታ ብረታና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር፣ በኮርፖሬሽኑ የሃይቴክ ኢንዱስትሪ ሥራ አስኪያጅ የቦርድ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የኮርፖሬሽኑ የሥነ-ምግባርና የሕግ ጉዳዮች ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳኋን በመምራት ከግዥ መመሪያ ውጭ ጥራታቸውን ያልጠበቁ 11 ራዳሮችን ከ214 ሚሊየን ብር በላይ በሆነ ወጪ በመግዛት በመንግስት ላይ ጉዳት በማድረስ በከባድ የሙስና ወንጀል በሚል ነበር ክሱ የቀረበው።

ተከሳሾቹ በ2004 ዓ.ም በኮርፖሬሽኑ የግዥ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የግዥ ፈፃሚው አካል ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ጥራት ባለው በተቀላጠፈና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በተወዳዳሪ ዋጋ በጨረታ መፈፀም ሲገባቸው፥ መመሪያውን ወደ ጎን በመተው ያለጨረታ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የግዢ ፍላጎት ሳይጠየቅ ሴሌክ እና አሊት ከተባሉ የቻይና ኩባንያዎች ተመሳሳይነት ያላቸውን 11 ራዳሮች መግዛታቸውን እና ራዳሮቹ አገልግሎት ሳይሰጡ መቀመጣቸው በክሱ ተብራርቷል።

ከኮርፖሬሽኑ የግዢ መመሪያ ውጪ ያለጨረታና ያለግዢ ፍላጎት 2ኛ ተከሳሽ ሴሌክ ከተባለው ኩባንያ ጋር የገባውን ውል እንዲያፀድቅ ለ1ኛ ተከሳሽ ደብዳቤ የጻፈ በመሆኑ እና 1ኛ ተከሳሽ ውሉን በማጽደቅ በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሳሾች በኩል የተፈረሙት ውሎች ጨረታ ሳይደረግ እና የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የግዢ ፍላጎት ሳይጠይቅ የተፈጸመ መሆኑ እንዲሁም ውሉ ያለአግባብ እንዲፀድቅ መደረጉ በክሱ ተጠቅሷል።

በዚህ መልኩ የቀረበውን ክስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ ወንጀል ችሎት ክሱን በችሎቱ ላይ በንባብ አሰምቶ እንደነበር ተገልጿል።

ሜጀር ጀኔራል ክንፈ ዳኘው በበኩላቸው በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸውን ጠቅሰው፥ የዕምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል። ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ለወንጀሉ መፈጸም ያስረዱልኛል ያላቸውን 8 የሰው እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ካቀረበ በኋላ ችሎቱ የምስክር ቃልን እና ማስረጃዎችን መርምሮ ሜጀር ጀኔራል ክንፈ ዳኘው በተከሰሱበት በወንጀል ህግ አንቀጽ 32 /1 ሀ እና አንቀጽ 411 ንዑስ ቁጥር 2 መሰረት እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቶ እንደነበር ተመላክቷል።

በዚህ መሰረት ሜጀር ጀኔራል ክንፈ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ እና የቀድሞ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ጀኔራል ሳሞራ የኑስን ጨምሮ ከ5 በላይ የሰው የመከላከያ ምስክሮችን እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበው ነበር። በተከሳሹ የቀረቡ የመከላከያ ማስረጃዎችን የመረመረው ፍርድ ቤቱ ማስረጃዎቹ የዐቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በተገቢው ማስተባበል አለመቻላቸውን አብራርቷል።

በዚህም ፍርድቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 149/1 መሰረት የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፎባቸዋል። የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ለመጠባበቅም ለሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ተቀጥሯል። በተመሳሳይ የራዳር ግዢ የሙስና ክስ በ5ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ጉዳያቸው ሲታይ የነበሩት የሜቴክ የሕግ ክፍል ኃላፊ የነበሩት ኮሎኔል መሐመድ ብርሃን አብርሃ የቀረበባቸውን ክስ በተገቢው ተከላክለዋል በሚል ከሁለት ሳምንት በፊት በነጻ መሰናበታቸው ተጠቁሟል።

በሌላ ርዕሰ ጉዳይ የቀድሞው የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ በ15 ተከሳሾች ላይ ከ348 ሚሊዮን ብር በላይ ህገ-ወጥ ግዥ በመፈፀም በሙስና ወንጀል እና በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ክስ ተመስርቶባቸዋል።

በኢፌዲሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ የቀድሞው የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ በ15 ተከሳሾች ላይ ከ348 ሚሊዮን ብር በላይ ህገ-ወጥ ግዥ በመፈፀም በሙስና ወንጀል እና በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ክስ መሰረተባቸው። ጉዳዩ የቀረበው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ችሎት ነው።

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ተከሳሾች 1ኛ ዶ/ር ጫላ ዋታ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት የነበረ፣ 2ኛ ዶ/ር ታምሩ ጣሞሌ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት የነበረ፣ 3ኛ ዶ/ር ሮባ ደምቢ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደር እና የተማሪዎች አገልግሎት ም/ፕሬዝዳንት የነበሩ፣ 4ኛ ኢ/ር አብርሃም ባያብል የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስ እና ተቋማዊ ልማት ም/ፕሬዝዳንት የነበረ፣ 5ኛ አቶ ሊበን ደሊሎ በቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የግዢ ዳይሬክተር፣ 6ኛ አቶ ቦሩ ህርጳዬ በቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የፋይናንስ ዳይሬክተር የነበረ፣ 7ኛ አቶ ለታ ድሪባ በቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ መምህር እና የቢ.ኤች.ዩ አማካሪ ድርጅት ተወካይ፣ 8ኛ አቶ አብራሃም ቡሶዋ በቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ፣ 9ኛ አቶ ተስፋሁን ሌጃቦ ተስፋሁን ሌጃቦ ጠቅላላ የግል ስራ ተቋራጭ ስራ አስኪያጅ፣ 10ኛ አቶ አያሌው ካሳ ቦኩ ኢቲያንሳ ጠቅላላ የግል ስራ ተቋራጭ ስራ አስኪያጅ፣ 11ኛ አቶ ጉተማ ቡሌ አዱላ ጠቅላላ የግ/ስ/ተቋራጭ ስራ አስኪያጅ፣ 12ኛ አቶ አንጂሎ አርሾ ጠቅላላ የግል ስራ ተቋራጭ ስራ አስኪያጅ፣ 13ኛ አቶ ለሚ ኤጀታ ቢዳሩ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ፣ 14ኛ አቶ አይመን አቡዱላሂ አረብ ኮንስትራክሽን ስራ አስኪያጅ፣ 15ኛ ወ/ሮ ፀሃይ ሀይሉ የመንግስት ስራ የሚሰሩ ሲሆኑ፤ በድምሩ በ15 ተከሳሾች ላይ የእያንዳንዳቸው የተሳትፎ ደረጃ ተጠቅሶ በዐቃቤ ሕግ አራት ተደራራቢ ክሶች ተመስርቶባቸዋል።

በ1ኛ ክስ ላይ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ባሉት ተከሳሾች ላይ ሲሆን፤ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉ ተከሳሾች ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራር እና የማናጅመንት አባል በመሆን የተሰጣቸዉን ከፍተኛ የስራ ሃላፊነት በመጠቀም በሚሰሩበት ወቅት 7ኛ እና 8ኛ ተከሳሾች እንደቀደም ተከተላቸው የBHU Consulting Engineers General Level ድርጅት ቢሮ አስተባባሪ እና የቦርድ አባል ሆነው ሲሰሩ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት እና በመንግስት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፥ የመንግስት የግዥ አዋጅ እና አፈጻጸም መመሪያን በመጣስ በ1ኛ ተከሳሽ ስም ለተመዘገበውና ህገ-ወጥ ከሆነው ቢ.ኤች.ዩ አማካሪ ድርጅት ጋር

ከምርመራ ማህደር ... ወደ ገጽ 11 የዞረ

# የተቋማት የግዥ ስርዓትና...

አቅራቢ በቅድሚያ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ዓይነት በዝርዝር ሲያቀርብ በግምገማ የተሻለ ዝርዝር መረጃ ያቀረበው አቅራቢ ለፋይናንስ ውድድር እንዲቀርብ ይደረጋል። በዚህ ግዥ ዘዴ ለአቅራቢ የሚፈለገውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነት ዝርዝር መረጃ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ሌሎች ያልተሰጠውን የተቋሙን የፍላጎት መረጃ ለተፈላገው አቅራቢ በመስጠት ለግዥው አሸናፊ እንዲሆን በማመቻቸት ሙስና ይፈፃማል።

በመጨረሻም የምናየው በውል አስተዳደር ላይ የሚከሰት ሙስና ነው። በውል አስተዳደር ውስጥ ለግዥ ከተወዳደሩት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ከሆነው አቅራቢ ጋር የሚፈጸም የውል ስምምነት መሠረት ክትትል የሚደረግበት አሠራር ነው። የግዥ አሸናፊ አቅራቢዎች ልየታ ሂደት ላይ አንዳንድ ጊዜ ያለበቂ መመዘኛ መስፈርት አሸናፊ ለተደረገው አቅራቢ ላይ ቅሬታ መቀበልና ምላሽ መስጠት ሲገባ፥ የቀረበውን ቅሬታ ወደኋላ በመተው ወይም በቂ ምላሽ ሳይሠጥ አሸናፊ ከተባለው አቅራቢ ጋር በተገባው ስምምነት ቅድመ ክፍያ የሚፈጸምበት አግባብ የሙስና ሥጋት መኖሩን አመላካች ነው። ሌላው የውል ስምምነት የፈጸመ አቅራቢ ጋር በሚደረግ በመመሳጠር አቅራቢው ከፈጸመው የውል ስምምነት መሠረት ሳይፈጸም ሲቀር ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድም በተመሳሰይ የሙስና ሥጋት እንዳለበት ያጠራጥራል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አቅራቢው በሚደረግ መመሳጠር ከውል ስምምነት ወጪ የሆነ ዕቃ የመረከብ ወይም አገልግሎት የማግኘት አሠራሮች መኖራቸው የሙስና ሥጋት መኖሩን ያመለክታሉ። በግዥ ህግና መመሪያ ላይ ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ ወይም ዋስትና ሳያቀርብ ቅድሚያ ክፍያ መፈጸም እንዲሁም የዕቃ ወይም አገልግሎት ርክክብ ሳይፈጸም የመጨረሻ ክፍያ መፈጸም የሙስና አመለካቾች ናቸው።

በመሆኑም ተቋማት በግዥ አፈፃፀም ላይ የሚከሰተውን ሙስና እንዴት መከላከል ይችላሉ። በተቋማት የሚፈጸም ሙስና ለመከላከል ቅድሚያ ሚና ያለው የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ይሆናል። የበጀት ዕቅድ ሲታቀድ ለምን ዓላማ እንደታቀደ በቂ መረጃ ማግኘትና የታቀደው በጀት የተቋሙ ተልዕኮ ከማሳካት አንፃር ያለውን ስብጥርና ግንኙነትን በየጊዜው በግልጽ መገምገምና አቅጣጫ ማስቀመጥ አለበት።

የበጀት ዕቅድ ከታቀደ በኋላ ለግዥ የተፈለገው ዕቃ ወይም አገልግሎት በቅድሚያ የግዥ ፍላጎት መረጃ ከሥራ ክፍሎች መሰብሰቡን፣ የተሰበሰበው መረጃ በተገቢ መንገድ መደረጃቱንና ይህንኑ የሥራ ክፍሎችና ማኔጅመንቱ ማረጋገጡንና ግዥው ሲፈጸም ለተቋሙ የሚሰጠውን ጥቅም በቅድሚያ መገምገምና በትክክል መረዳት ይጠበቃል። ለታቀደው ግዥ የትኛው የግዥ ዘዴ ጥቅም ላይ እንደሚውል በቅድሚያ የማረጋገጥ ሥልጣን የተቋም የበላይ ኃላፊ ሲሆን፥ ግዥውን የሚያስፈጽምና የሚያጣራ የወደኋላ ታሪካቸው ላይ ሥነምግባር ችግር የሌለባቸውን ሰዎች የያዘ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማዋቀርና አፈፃፀሙን በየጊዜ መገምገም ያስፈልጋል።

ሌላው የዲጂታል አሠራር ግዥ ዘዴን መጠቀም በዘርፉ የሚከሰተውን ሙስና እና ብልሹ አሠራር መቀነስ ነው። ግዥዎችን በዕቅድና በትግበራ መርሃ ግብር መሠረት በመንግስት የተዘረጋውን Electorinc Goverement Procurement (e-GP) በመጠቀም እንዲፈጸም የተቋሙ የበላይ አመራር ተገቢውን ክትትልና ግምገማ በቁርጠኝነት ማድረግና ማረጋገጥ ይጠበቃል።

የተገዙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የተቋሙን ተልዕኮ ከማሳካት አንፃር ያለቸውን ፋይዳ በየጊዜ ገንዘብ ሊያስገኝ ከሚችለው ጠቃሜታ አንፃር እየተገመገመ በታዩት ተግዳሮቶች ወይም ችግሮች ላይ ወቅታዊ መፍትሄ መስጠትን ይሻል። ከዚህ አንፃር በተቋሙ የክትትልና ቁጥጥር ሚና ያለቸው የህግ አገልግሎት የግዥ የውል አስተዳደር ሰነዶችን ማዘጋጀትና አፈፃፀሙን መከታተልና ሪፖርት በወቅቱ ማቅረብ፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ግዥው ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ቀዳዳ ከሚከፍቱ አሰራሮች በፀዳ መልኩ እየተፈጸመ መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ በመሥራት እንዲሁም የኦዲት አገልግሎት ደግሞ ግዥው የመንግስትን የግዥ ህግ፣ መመሪያና ማኑዋል ተከትሎ የሚፈጸም መሆኑ የመከታተልና የማረጋገጥ ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

ሌለው በተቋሙ ውስጥ ግዥ ሥራዎችን የሚፈጽሙ ባለሙያዎች በሥነምግባር እንዲታነፁ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተደጋጋሚ የአመለካከት ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የሥነምግባር ግንባታ ሥልጠና መስጠት፣ አመራርና ሠራተኞች የሚመሩበትን የሥነምግባር መመሪያ ማዘጋጀትና ግንዛቤ መፍጠር፣ የአፈፃጸም ውጤታማነትን በመከታተል በዕቅድ መከናወን አለበት።

የተቋም የበላይ አመራር የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያግዙ ግዥዎች ብቻ እንዲፈጸሙ ለማድረግ ግዥዎች ላይ ተገቢውን ክትትልና ግምገማ የማካሄድ ሥራን በትኩረት ማከናወን እንዲሁም በግዥ አፈፃፀም ሂደት ላይ የሚስተዋሉ የሥነምግባር ጥሰቶች ላይ አስፈላጊውን አስተማሪ የሆነ ወቅታዊ እርምጃ መውሰድ አለበት።

የተቋም የሥነምግባር መከታተያ ክፍልም በግዥ በተፈጥሮ እርጥብ የሥራ አካባቢ ላይ ሙስና የሚፈጸም እንደመሆኑ መጠን፥ በግዥ ሥራ ላይ ተመድበው የሚሠሩ ሰራተኞችና አመራሮች ባህሪያቸውንና ኑሮአቸው ላይ የሚታዩ ለውጦችን በየጊዜው በመከታተልና መረጃ የመያዝ፣ ከአቅራቢ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት መከታተልና መረጃ የመያዝ፣ የሙስና ወንጀልና ሊፈፀም የታሰበ ሙስና ችግር ካለ ጥቆማ ለመቀበል የሚያስችል አሰራር በግልጽ በመዘርጋት አፈፃፀሙ ውጤታማ እንዲሆን መከታተልን በዕቅድ ማከናወን ይጠበቃል።

# ከሙስና ምርመራ ማህደር ...

13 ሚሊዮን 478 ሺ 150 ብር በቀጥታ ግዥ የውል ስምምነት እንዲፈፀም እና ክፍያዎችም እንዲፈፀሙ በማኔጅመንት አለአግባብ ውሳኔ በማስተላለፍ፥ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉ ተከሳሾች በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ያልጸደቀ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 39/2012 የሚል በማውጣት እና በዚሁም ደንብ ድርጅቱ በማማከር የሚያገኘዉን ትርፍ ክፍፍልን በራሳቸው በመወሰን ከዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ቁጥር በተለያዩ ቀናት በድምሩ 23 ሚሊዮን 135 ሺ 433.27 ብር ተቀንሶ በህገ-ወጥ መንገድ ባቋቋሙትና በቀጥታ ግዢ የግንባታ የማማከር ስራዎችን ውል እንዲዋዋል ባደረጉት ቢ.ኤች.ዩ አማካሪ ኢንጂነርስ ድርጅት ስም በከፈቱት ሂሳብ ቁጥር እንዲተላለፍ ካደረጉ በኋላ በ1ኛ እና 6ኛ ተከሳሽ ፊርማ፥ ለ1ኛ ተከሳሽ 2 ሚሊዮን 116 ሺ 16.65 ብር፣ ለ2ኛ ተከሳሽ 542 ሺ 705.82 ብር፣ ለ3ኛ ተከሳሽ 523 ሺ 47.60 ብር፣ ለ4ኛ ተከሳሽ 2 ሚሊዮን 82 ሺ 747.14 ብር፣ ለ5ኛ ተከሳሽ 99 ሺ 284.67 ብር ለ6ኛ ተከሳሽ 421 ሺ 78.67 ብር፣ ለ7ኛ ተከሳሽ 1 ሚሊዮን 467 ሺ 185.84 ብር፣ ለ8ኛ ተከሳሽ 324 ሺ 20.72 ብር በተለያዩ ቀናት በስማቸው በተከፈተ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ቁጥር አለአግባብ ገቢ የሆነላቸው እና አለአግባብ እንዲከፋፈል ያደረጉ በመሆኑ፥ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን በፈፀሙት ስልጣንን አለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል።

2ኛ ክስ ከ1ኛ እስከ 6ኛ፣ 8ኛ፣ 9ኛ፣ 10ኛ እና 11ኛ ባሉት ተከሳሽ ላይ ሲሆን፥ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉ ተከሳሾች የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ አመራርና ማኔጅመንት አባል በመሆን የመንግስት የግዥ አዋጅ እና አፈጻጸም መመሪያን በመተላለፍ በቀን ሰኔ 10/2012 ዓ.ም በያዙት ቃለ-ጉባኤ በቀጥታ ግዥ እንዲፈጸም ውሳኔ በማስተላለፍ በግዥ ህግ አግባብ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ በውድድር መሰጠት ያለበትን ስራ ያለምንም ጨረታ በቀጥታ ግዥ በድምሩ 195 ሚሊዮን 52 ሺ 812.81 ብር ግዥ ያለአግባብ እንዲሰጥ በማድረግ በመንግስት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ በመሆኑ፤ 8ኛ ተከሳሽ የዩኒቨርሲቲው ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ከስራ ተቋራጮቹ ጋር በጋራ ከሚያስተዳድረው ገንዘብ አለአግባብ ለ1ኛ ተከሳሽ ጥቅም ወጪ እንዲሆን በቼኮቹ ላይ የፈረመ እና 1ኛ ተከሳሽ ከስራ ተቋራጮቹ ባለቤት እና ተወካይ ከሆኑት 9ኛ፣ 10ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች ጋር አለአግባብ ውል በመዋዋል እና የማይገባው ጥቅም በመውሰድ እንዲሁም ከ9ኛ እስከ 11ኛ ያሉ ተከሳሾችም ከ1ኛ እስከ 6ኛ ካሉ ተከሳሾች ጋር በጥቅም በመመሳጠር ያለምንም ጨረታ በቀጥታ ግዥ ውል በመዋዋል ያለአግባብ ጥቅም ያገኙ እና በመንግስት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ በመሆኑ በዋናና በልዩ ወንጀል ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በስልጣን አለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል።

3ኛ ክስ ከ1ኛ እስከ 6ኛ፣12ኛ፣ 13ኛ እና 14ኛ ባሉት ተከሳሾች ላይ ሲሆን ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉ ተከሳሾች የመንግስት የግዥ አዋጅ እና አፈጻጸም መመሪያን በመጣስ ያለአግባብ 14 ተሽከርካሪዎችን እና ማሽነሪዎችን በቀጥታ ግዥ እንዲፈፀም በመወሰን መንግስት የሚያገኘውን ጥቅም በማሳጣትና ጉዳት በማድረስ እንዲሁም የግዥው ህገ-ወጥነት እንዳይታወቅ ዩኒቨርሲቲው ለመሰረተ ልማት ግንባታ በተፈቀደለት ካፒታል በጀት ውስጥ በማካተት በድምሩ 116 ሚሊዮን 389 ሺ 964.18 ብር ግዥ እንዲፈፀም ያደረጉ ሲሆን፤ 12ኛ፣ 13ኛ እና 14ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾችም በህገ-ወጥ የተሽርካሪ ግዢ አለአግባብ ጥቅም ያገኙ በመሆናቸዉ በዋናና በልዩ ወንጀል ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በስልጣን አለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል።

4ኛ ክስ በ1ኛ እና በ15ኛ ባሉት ተከሳሾች ላይ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ የመንግስት የግዥ አዋጅ እና አፈጻጸም መመሪያን በመጣስ ያለምንም ጨረታ በክስ 1፣ 2 እና 3 ቀጥታ ግዥ እንዲከናውን በማድረግ፣ እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው እና ከድርጅቱ ሂሳብ ቁጥር ተቀናሽ ተደርጎ ወደ 1ኛ ተከሳሽ ህጋዊ ባለቤት ወደሆነችው 15ኛ ተከሳሽ 10 ሚሊዮን ብር ገቢ ያደረጉ ሲሆን፥ 15ኛ ተከሳሽም ገቢ የተደረገላትን 10 ሚሊዮን ብር የመኖሪያ ቤት ህንፃ ግዥ ክፍያ እንዲውል መኖሪያ ቤቱን ወደ ሸጠው ግለሰብ በተለያዩ ባንኮች ያስተላለፈች በመሆኑ እንዲሁም 1ኛ ተከሳሽ 1 ሚሊዮን ብር ህጋዊ በማስመሰል ህጋዊ ባለቤቱ ለሆነችው 15ኛ ተከሳሽ ገቢ ያደረገ እንዲሁም 500 ሺ ብር በጉዱ ጀነራል ትሬዲንግ ህጋዊ በማስመሰል ለአክሲዮን መግዣ እንዲውል ያስተላለፈ በመሆኑ፥ በአጠቃላይ 1ኛ እና 15ኛ ተከሳሾች ምንጫቸው የሙስና ወንጀል የሆነ ገንዘብ ህጋዊ በማስመሰል የተጠቀሙበት፣ ያዘዋወሩ፣ ያስተላለፉ እንዲሁም በህገ-ወጥ መንገድ የተገኘውን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስለው በማቅረብ በዋና እና በልዩ ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙበት በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከሰዋል።

ሌላው “መሬት እናሰጣለን” በማለት ከ10 ሚሊየን ብር በላይ ሙስና ተቀብለዋል በተባሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሦስት ሠራተኞች ላይ ክስ የመመስረቻ ጊዜ ተፈቀዷል።

ተጠርጣሪዎቹ፥ 1ኛ የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት የግንባታ ቁጥጥር ባለሙያ ፍቅረስላሴ ታደለ፣ 2ኛ የቀድሞ የአዲስ አበባ ከተማ ከተማ አስተዳደር የአቤቱታና ቅሬታ ምርመራ ዘርፍ ዳይሬክተር ታምራት እስጢፋኖስን እና የየካ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር የመብት ፈጠራ ቡድን መሪ ዘውዱ ደገፋ ይባላሉ።

መርማሪ ፖሊስ በተጠርጣሪዎቹ ላይ ሲያከናውን የቆየውን ምርመራ መዝገብ ለዓቃቢ ህግ ማስረከቡን ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አስታውቋል።

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሪክቶሬት ዓቃቢህግ ተጠርጣሪዎቹ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አራራት ሆቴል ጀርባ “5 ሺህ ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ እንሰጣለን” በማለት አስቀድመው 30 ሚሊየን ብር ሙስና ገንዘብ ከጠየቁ በኋላ ከሁለቱ የግል ተበዳዮች 10 ሚሊየን 250 ሺህ ብር ተቀብለዋል ሲል ባቀረበው የጊዜ ቀጠሮ መጠየቂያው ላይ አብራርቷል።

በተጨማሪም 1ኛ እና 2ኛ ተጠርጣሪ የሜሪዲያን ሆቴል ባለቤት ለሆኑት ግለሰብ በሆቴሉ ስም የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመከነ ቢሆንም፥ በይዞታው ላይ 1ሺህ 600 ካሬ ሜትር ጭማሪ እንደተደረገላቸው የሚያሳዩ የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን ለግል ተበዳይ ማሳየታቸውን ጠቅሶ ዓቃቢህግ የጊዜ ቀጠሮ መጠየቂያው ላይ አስረድቷል።

በዚህ መልኩ ተጠርጣሪዎቹ ሲገለገሉበት ቆይተዋል የተባሉበትን ሀሰተኛ የከተማ አስተዳደሩ ሰነዶችን በ1ኛ ተጠርጣሪ መኖሪያ ቤትና 2ኛ ተጠርጣሪ በሚያሽከረክረው ተሽከርካሪ ውስጥ በብርበራ መገኘቱን እንዲሁም በ1ኛ ተጠርጣሪ መኖሪያ ቤት ህገወጥ የጦር መሳሪያዎች የተያዙ መሆኑን ዓቃቢህግ ለጊዜ ቀጠሮ አቅርቧል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የ15 ቀን ክስ የመመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠውና ተጠርጣሪዎቹ በማረፊያ ቤት እንዲቆዩለት ዓቃቢ ህግ ጠይቋል።

ተጠርጣሪዎች በበኩላቸው፥ ተጨማሪ ጊዜ መሰጠት የለበትም፥ የዋስትና መብታችን ሊከበር ይገባል የሚሉ መከራከሪያ ነጥቦች ተነስተዋል።

ክርክሩን የተከታተለው የጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ተጠርጣሪዎች ያቀረቡትን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በስነ-ሥርዓት ህጉ መሰረት የ15 ቀን ክስ የመመስረቻ ጊዜ ለዓቃቢ ህግ ፈቅዷል።

በዚሁ ወር ከ15 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት የኤክስፖርት ቡና የጫነ ተሽከርካሪን በማገት ቡናውን ወስደዋል በተባሉ 11 ግለሰቦች ላይ ክስ ተመስርቷል።

ከ15 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት የኤክስፖርት ቡና የጫነ ተሽከርካሪን መንገድ በመዝጋት አስፈራርተው ቡናውን ወስደዋል በተባሉ 11 ግለሰቦች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቷል።

የኤክስፖርት ቡና የጫነ ተሽከርካሪን በማገትና በማራገፍ ግማሹን ቡና በመሸጥ ለግል ጥቅም አውለዋል የተባሉ ተከሳሾች ናቸው ስልጣንን ያለአግባብ በመገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ የተመሰረተባቸው።

ክሱ የተመሰረተው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ነው። ተከሳሾቹ የመከላከያ አባል ነው የተባለው ሻንበል ዜና ማርቆስ አለሙ፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አባል የሆነው ትንሳኤ ታከለ እና የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት አባል የሆነው ታምራት ጌታቸውን ጨምሮ አጠቃላይ 11 ግለሰቦች ናቸው።

ከነዚህ ተከሳሾች መካከል ከ7ኛ እስከ 11 ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተከሳሾች በግል ስራ ላይ የሚተዳደሩ መሆናቸው ተጠቁሟል።

ተከሳሾቹ በጥቅም በመመሳጠር በመጋቢት ወር 2015 ዓ/ም በተለያዩ ቀናት ኤክስፖርት የሚደረግ ቡና ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጣ በስልክ በመደዋወልና መረጃ በመለዋወጥና በመነጋገር ተሽከርካሪውን አስቁመው ለመውሰድ በመስማማት ዝግጅት ማድረጋቸው በክሱ ተመላክቷል። በዚህ መልኩ ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ከሲዳማ ክልል ዳዬ ቦንሳ ዳዬ ከተማ እና ዳሌ ወረዳ ማንቼ ቀበሌ መነሻቸውን ያደረጉ ኤክስፖርት ቡና የጫኑ ሁለት የጭነት ተሽከርካሪዎችን ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ በመኪና በመከተል በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 06 አካባቢ ተሽከርካሪዎቹ ላይ መንገድ በመዝጋት እና በማስቆም ሾፌሮችንና ረዳቶችን ማስወረዳቸው ተጠቁሟል።

ሾፌሮችንና ረዳቶችን በማስፈራራት እና በቁጥጥር ስር እንደዋሉ በመግለጽም ቡናውን የጫኑ ተሽከርካሪዎችን በሌላ አሽከርካሪ በመውሰድ 10ኛ ተከሳሽ በተከራየበት መጋዘን ውስጥ ቡናውን አራግፈው መኪናውን ጉለሌ ክ/ከተማ ሩፋኤል አካባቢ አቁመው መሄዳቸው ተጠቅሷል።

በዚህ መልኩ ከ338 ኩንታል በላይ ከታጠበ ቡና ውስጥ በፍ/ቤት ትዕዛዝ በተደረገ ብርበራ 135 ኬሻ የታጠበና የተበጠረ ቡና እንዲሁም ሌላ 33 ነጥብ 5 ኬሻ ደግሞ የታጠበ ቡና በ10ኛ ተከሳሽ መጋዘን ውስጥ ተደብቆ የተገኘ ሲሆን ፥ቀሪው ቡና ግን ተሸጦ ለግል ጥቅም መዋሉ በክሱ ተመላክቷል። እንደ አጠቃላይ የተከሳሾችን ተሳትፎ በዝርዝር ጠቅሶ 3 ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦባቸዋል።

# ኪነ-ጥበብ

**ከፈጣሪ በታች ህሊና ዳኛ ነው!**

## ማነህ ማነሽ እኛ ማነን?

የሠው ማንነቱ፣ ሚዛኑ መለኪያው፥
ስነምግባሩ ነው፣ መልካም ስብዕናው።
ሲመዘን ሲፈተሽ፣ የውስጥ ማንነቱ፤
ሊገልፀው አይችልም፣ ውጫዊ ውበቱ።

ዛፍ ከፍሬው ነው፣ ሊለይ የሚችለው፤
ያልሆነውን ሊያበቅል፣ አይችልም ተፈጥሮው።
መራራ ከሆነ፣ ፍሬውም ይመራል፥
ጣፍጭም ከሆነ፣ ፍሬው ይጣፍጣል፤

ያንተም፣ ያንቺም፣ የኛም፣ የሁላችን ፍሬያችን፥
ምንድን ነው ስነምግባራችን፤
ማነህ ማነሽ እኛ ማነን?
ሠው ነና፣ ብቻ መልስ አይሆንም።
መልካም ስብዕና፣ ትህትና ያለው፤
ለራሱ፣ ለጥቅሙ ብቻ የማይኖረው።
ትጉህና ታማኝ፣ ስራውን አክባሪ፥

ለሀገር ለትውልድ፣ አርቆ አሳቢ፥
በዕውነት የታነፀ፣ የፍቅር ምሳሌ፥
ተግበሩ በጎነት፣ ተፅኖ ፈጣሪ።
ማነህ ማነሽ እኛ ማን ነን?

እራሳችንን እንይ፣ የቱ ጋር እንደሆንን፤

ወይስ በገንዘብ፣ በጥቅም ተደለን፥
አድሎኛ ሆነናል፣ ፍትህ እያዛባን፥
ሠው አየን አላየን፣ ብለን የምንሰራ፥

ቅንነትን ጥለን፣ ለጋሚ ዳተኛ።
በቀለም በብሄር፣ በዕምነት በፆታ፥
በዘር ፖለቲካ፣ ሠውን ምንለካ፥

ማነህ ማነሽ እኛ ማን ነን?

እራሳችንን እንይ፣ የቱ ጋር እንደሆን፥
ለሁሉ እኩል ይሁን፣ መመሪያ ደንባችን፤
ፊት አይተን አናድላ፣ ፍትሃዊ እንሁን።

**በታሪኳ ግርማ**

# መልካም ዜና

## ስለ ራሷ ሳይሆን ስለ ሰው የኖረች

ወ/ሮ ሙዳይ ምትኩ

አንዳንድ ሰው ለራሱ ከመኖር አልፎ ለሌሎች አለኝታ በመሆን የሥነምግባራዊ ህይወት አስተማሪ፣ የመልካም ተግባራት ተምሳሌት ይሆናል። በዚህ ዘመን በማህበራዊ ህይወታችን የምንሰማው ሰቅጣጭ ነገሮችን የሚፈጽሙ ግለሰቦች እንዳሉ ሁሉ በተቃራኒው በፍጹም ሰባዊነት ህይወታቸውን ሳይሳሱ ለሌሎች የሚሰጡም አሉ። ለዚህም ማሳያነት የበጎነትን ጥግ የምታሳን፣ ስለ ራሷ ሳይሆን ስለ ሰው የኖረች የሙዳይ በጎ አድራጎት ድርጅት መስራች ሙዳይ ምትኩ ትባላለች የጎዳና ህፃናት ወላጅ የሌላቸው በበሽታ የተጠቁትን ህፃናት ከየጎዳናው በማሰባበሰብ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ፊት ለፊት ባለው በኪራይ ቤት ሙዳይ የበጎ አድራጎት ድርጅት በመክፈት ስለ ራሷ ኑሮ ትዳሯን ልጆቿን ብቻ ሳታስብ ለብዙሀን የምትኖር ዘር ሀይማኖት ብሔር ሳትለይ በተለያዩ እደ ጥበብ በባህል ልብስ፤ ስካርቭ ፤ቦርሳ ፤የባህል የሸክላ መመገቢያዎችና የቤት ጌጣ ጌጦችን በመስራትና በመሸጥ ብዙ ቤተሰብ የሌላቸው ህፃናት የምታሳድግ የምታስተምር አስተምራም ለቁም ነገር እያበቃች ያለች የበጎነት ተምሳሌት የብዙሀን እናት ናት። ወደ እዚህ የበጎነት ስራ እንዴት እንደገባች ስትናገር የሁለተኛ ትምርቷን እንደጨረሰች ከጓደኛዋ ጋር በመሆን ትምህርት ቤት ታቋቁማለች። ከስራ ወደ ቤቷ ስትመለስ ጎዳና ላይ በልመና ከሚተዳደሩ ወላጆቻቸው ጋር የሚውሉ ህጻናትን ስታይ ግን መክፈል አይችሉም ብላ አልተወቻቸውም።

የችግረኛና ጎዳና ላይ በልመና የሚተዳደሩ ወላጆች ልጆችንና በተለያዩ የአካልና የአእምሮ እክል ሳቢያ መክፈል ቢችሉም ከሌሎች ህጻናት ተገልለው የትምህርት ዕድል የተነፈጋቸውን ህጻናት ሁሉ አሰባስባ መክፈል ለማይችሉት በሯሷ ወጪ ዩኒፎርም አሰፍታ በነጻ ታስተምራቸው ጀመር።

ይህ በጎ ተግባር ግን ውሎ አድሮ በትምህርት ቤቱ ልጆቻቸውን ከፍለው በሚያስተምሩት ወላጆች ዘንድ ተቃውሞን ቀሰቀሰ። ልጆቻችን ወላጆቻቸው ጎዳና ላይ በልመና ከሚተዳደሩ ሰዎች ልጆች ጋር መማራቸው ለበሽታ ይዳርጋቸዋል' ያሉ በርካታ ወላጆች ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤቱ አስወጥተው ወደ ሌላ ትምህርት ቤት እንደሚያስገቡ በመግለጽ ወይ የእኛን ልጆችና ብር አልያም የድሆቹን ልጆች ምረጪ አሏት። የደሀዎቹን ልጆች መረጠች።

በርካታ ወላጆች ልጆቻቸውን ከትምርት ቤቱ ሲያስወጡ ጥቂት የሚከፍሉ ወላጆች ልጆች ብቻ ቀሩ። በጥቂት የሚከፍሉ ወላጆች ክፍያ ብቻ ትምህርት ቤቱን ማስተዳደር እየከበደ ቢመጣም ወ/ሮ ሙዳይ ግን የከፋውን ችግር በርጋታ አሳለፈችው። ቀስ በቀስ ግን ወ/ሮ ሙዳይ ለትርፍ ብላ ከጓደኛዋ ጋር ያቋቋመችውን ይህን ትምህርት ቤት የእርዳታ ድርጅት አድርጋው በርካቶችን እየረዳችበት ነው።



በአቋራጭ የህይወት ጥሪን ማግኘት ይሏል ይህ ነው።ሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር ከ19 ዓመት በፊት የተቋቋመ ሲሆን፥ በአሁኑ ወቅትም 614 ልጆች እና 450 እናቶችን በተለያየ ሁኔታ በመደገፍ ላይ ይገኛል። ከ614 ልጆቹ ውስጥ 150ዎቹ በማህበሩ ግቢ ውስጥ የሚውሉ፣ የሚማሩ እና የሚያድሩ ናቸው፤ እናቶች ደግሞ የሸክላ ቅርጻ ቅርጽ፣ የሽመና እና የልብስ ስፌትን ጨምሮ የተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎች እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

---

## ያገኙትን 200ሺ ዶላር የመለሱ ኢትዮጵያዊ

አቶ አማራ ታደሰ ይባላሉ፤ በቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት የቢዝነስ ክላስ ላውንጅ ባርማን ናቸው። የአንድ ናይጄሪያዊ ምንገደኛ ተረስቶ ያገኙትን 200,000 ዶላር ለባለቤቱ መልሰዋል። አቶ አማረ ታደሰ በኢትዮጵያ አየርመንገድ ለ32 አመት አገልግለዋል።

